# ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ

ፈቃደኞች ከሆናችሁ፡ እንደቆማችሁ፡ ለጸሎት ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ።

2 የሰማይ አባት ሆይ፡ በዚህ ምሽት ሌላ ዕድል አግኝተን፡ ይህን አስደናቂ እና ድንቅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን ማቅረብ መቻላችን፡ እጅግ እናመሰግናለን። ትላንትና፡ ዛሬ፡ እና ለዘላለም ያው ሆኖ ስለሚኖር እናመሰግንሃለን። በዚህ ቅዝቃዜ ወቅት እዚህ ስለ ተሰበሰቡት እና አሁንም አንዳች፡ ታላቅ የሆነ ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ፡ እንደሚሰጣቸው በማመን በታላቅ ጉጉት ስለሚጠባበቁ፡ ስለ እነዚህ ሰዎች እናመሰግናለን። ጌታ ሆይ፡ ያንን ተስፋ ይዘን፡ ወደ ጉባኤዎቹ ሁሉ እንመጣለን። ከባለፈው ማታ በፊት፡ በዚህ ተበርናክል ስለነበረው፡ ስለ አገልግሎትህ እናመሰግንሃለን፥ ባለፈው ምሽት ስላገለገልከው አገልግሎት፡ እና በዚህ ተበርናክል ስለሚኖር ስለ ዛሬ አገልግሎት፡ እናመሰግንሃለን። ዛሬ ማታ ምን እንደምታደርግልን አሁን እየጠበቅን ነው።

3 አባት ሆይ፡ እጆቹን ማንቀሳቀስ የሚችል ማንኛውም ሰው የመጽሐፍ ቅዱስን ገጾች መክፈት እንደሚችል እናውቃለን፡ ነገር ግን ቃሉን እውነት እና ህያው ማድረግ የሚችል አንድ አካል እንዳለ እናውቃለን፡ እሱም አንተው ነህ። እና፡ አባት ሆይ፡ ዛሬ ማታም እንዲሁ ታደርግልናለህ ብለን አንተን እንጠባበቃለን። በሁሉም መንገድ ባርከን። ለነዚህ ሁሉ ዓመታት የምንወደውንና የኖርንለትን እርሱን፡ ፊት ለፊት፡ ለማየት ጊዜው እየቀረበ መሆኑን ስናይ ልባችን በደስታ ይሞላል።

4 ጌታ ሆይ፡ ብዙዎች፡ ጌታን ተቀብለዋል። ትናንት ማታ ከነበረው ጉባኤ ብቻ፡ አርባ ወይም አምሳ የሚሆኑ፡ ጥዋት ላይ በስምህ ለመጠመቅ፡ ታላቅ ዝግጅት፡ እየተደረገ ይገኛል። አምላክ ሆይ፡ አቤቱ፡ ይህን እንድታስቀጥል እንጸልያለን፡ አስቀድሞ የተወሰነ የእግዚአብሔር ዘር ሁሉ የወንጌልን ብርሃን አይቶ፡ ወደ መንጋው እስኪገባ ድረስ ይህን እንድትቀጥል እንጸልያለን።

5 ዛሬ ማታ ስለ ዓለም ነገሮች አሳውረኸን፡ ኢየሱስን ማየት እንችል ዘንድ፡ ከቃል ጀርባ እንድትሰውረን እንለምንሃለን። ዛሬ ማታ፡ ከኢየሱስ ብቻ በቀር ማንንም የማናይበት፡ የደብረ ዘይቱ የመለወጥ ተራራ ልምምድ ይሁንልን። ስለ ክብሩ እና ስለወንጌሉ ማረጋገጫ፡ በስሙ እንለምናለን። አሜን።

አረፍ አረፍ በሉ።

6 ምንም ችግር ከሌለው፡ ይህን ማይክ፡ ወይም ይህን ዴስክ፡ ትንሽ ወደጎን አዞረዋለሁ፡ የጉባኤው ሁለቱ ጫፎች ማየት እንድችል። እነዚህን ማይክሮፎኖች እዚህ አካባቢ ማድረግ እንደምችል እገምታለሁ። እሺ፡ አንዴ።

7 ዛሬ ማታ፡ ከዋናው አዳራሽ ሰላምታ እናቀርብላችኋለን፡ በአሪዞና፡ ካሊፎርኒያ፡ ቴክሳስ፡ እና በመላው ዩናይትድ ስቴትስ ያላችሁ ወዳጆቻችንም፡ በስልክ መስመር ሰላምታችን ይድረሳችሁ። የዛሬ ማታ አገልግሎት፡ በስልክ መስመር ውስጥ፡ በ—በመላ-አገሪቱ ይሰራጫል፡ ስለዚህ እግዚአብሔር እንደሚረዳን እናምነዋለን።

8 ከአዳራሹ ከኋላ—በግራ በኩል ያላችሁ፡ ይሰማችኋል? እሺ፡ አሁን በትክክል እየሰራ መሆኑን ለማየት፡ የሰልክ መሰመሩን ይፈትሹታል።

9 በዚህ ምሽት ሁላችሁም ደስተኞች ናችሁ? [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ይሁን፡ ጥሩ ነው! **በዚህ** በኩል? ["ኣሜን።"] አሜን። ሁላችሁም በምቾት እንደተቀመጣችሁ በማየቴ በጣም ደስተኛ ነኝ።

10 አሁንም ነገ ማታ፡ እዝቡ እየጨመረ ከሄደ፡ በሰልክ መሰመር የሚተላለፍ ይሆናል። ዛሬም አለ። አንዳንዶች በዚያ ወደ ተበርናክሉ የሄዱ ይመስለኛል።

11 እና፡ ነገ ጠዋት፡ አገልግሎቶቹ በተብርናክሉ ውስጥ አይደረጉም፡ ምክንያቱም... ቤተክርስቲያኑን ነገ ከሰአት በኋላ ለሚደረግ ለሠርግ ስነ ሰርዓት የሚያሰጌጥ የአበባ ባለሙያ ይኖራል። ሰለዚህ የማለዳው—አገልግሎቶች፡ ወደ ወንድም ሩደል ቤተክርስቲያን፡ አስተላልፈውታል፡ እዚህ በአውራ ጎዳናው 62—ላይ የሚገኝ፡ ከባልደረቦቻችን መካከል አንዱ ነው። ይፋ ተደርጓል? [ወንድም ኔቪል "አዎን፡" አለ።—አርታዒ።] ይፋ ሆኗል። እና፡ በዚያም ሰው ቢበዛ፡ ሌሎቹን ክላርክሰቪል ወደሚገኘው አገልጋይ፡ ወደ ወንድም ጁኒየር ጃክሰን እንልካቸዋለን። በወንድም ሩዴል ያደረግንበት ምክንያት፡ ቅርብ ሰለሆነ፡ እና በቀላሉ... ያንን ማግኘት እንድትችሉ አሰበን ነው። በሆነ መንገድ እንዲፈጸም እናደርጋለን። የጥምቀት ሰነ ሰርዓቶች በሙሉ መፈጸማችሁን እርግጠኞች ሁኑ፡ እና ነገ በሚጠመቁ ሰዎች ላይ መቶ ወይም ሁለት እንደሚጨመሩ ተሰፋ አደርጋለሁ። እና አሁን ነገ ምሽት...

12 መናገር የምፈልጋቸው ነገሮች አሰቀድሜ ማስታወቂያ መናገር መቼም አልወደውም፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጉባኤ፡ ወይም አንድ ቀን፡ **ይህ መልከ ጼዴቅ ማን ነው?** በሚል ርዕሰ ጉዳይ ላይ መናገር እፈልጋለሁ፤ ምክንያቱም፡ በእነዚህ መገለጦች ዘመን ላይ እየኖርን እንዳለን አሰባለሁና፡ እነዚህም በዘመናት ሁሉ ጥያቄ ሆነው የቆዩ ናቸው፡ ይህም፡ "ይህ ሰው ማነው?" እርሱ ማን እንደነበረ፡ እግዚአብሔር መልሰ እንዳለው አምናለሁ። አንዳንዶች፡ "ካህን" ይላሉ፡ ሌሎችም "ንጉስ፡" ነበር ይላሉ፡ ጥቂቶች... ደግሞ...

13 ጥያቄ እሰካለ ድረሰ፡ ለጥያቄው መልሰ ሊኖር ይገባል፡ ይህም ትክክል ነው። መልሰ የሌለው ከሆነ ከጅምሩ ጥያቄ ሊሆን አይችልም።

14 አሁን፡ ሰናነበው፡ እግዚአብሄር በዚህ ምሽት ከቃሉ በረከት እንደሚሰጠን እናምናለን።

15 እና ሌላው ደግሞ... ቢሊ እዚህ ካሉት ህዝቦች ጋር ጥሩ ትብብር ማድረጋችሁን እንድነግራችሁ ተናግሮኛል ይህ ማለት በፓርኪን ሰርዓት፡ እና ከፖሊሶች ጋር እና ሌላው ሁሉ ነው። ቀጥሉበት፥ ያ እጅግ፡ እጅግ ድንቅ ነው።

16 ምናልባት በቅርብ ጊዜ ውስጥ፡ ዳሱን ወደ ከተማው ማምጣት የምንችልበትን ጊዜ፡ ለማየት ተሰፋ እናደርጋለን እና እዚህ ለተወሰነ ጊዜ ተክለን መቆየት በምንችልበት፡ ቦልፓርክ ውስጥ እንተክለዋለን፡ ምናልባት ለሦሰት ወይም ለአራት ሳምንታት፡ ተከታታይ፡ ሪቫይቫል። እና እዚህ ብዙም አንተዋወቅም፡ በዚህም ምክንያት ቻው-ተባብለን እንሄዳለንና። አሁን ግን መጥቼ ሰፊ ጊዜ መቆየት እፈልጋለሁ፡ ያን ጊዜ መቆየት እንችላለን በአንድ ወይም በሁለት ሌሊት መዝጋት አይጠበቅብንም፡ ነገር ግን ጊዜ ወሰደን፡ ቀንና ሌሊት፡ ቀንና ሌሊት እንማራለን፡ ይቀጥላል። ምናልባት አንድ ሰው ወደ ቤት ሄዶ

ዶሮዎችን መግቦ፡ ላሞችን አልቦ፡ በሚቀጥለው ሳምንት ተመልሶ በአገልግሎቱ ይገኛል። ያ—ደስ ይላል። ስለዚህ ጌታ ከእናንተ ጋር ይሁን።

17 አሁን፡ ከመሄዴ በፊት፡ ምናልባት እሁድ ጥዋት ወይም እሁድ ምሽት፡ ወይም በሆነ ጊዜ፡ ከእነዚህ አገልግሎቶች በአንደኛው ላይ፡ ሁላችሁም ስለ **ጋብቻ እና ፍቺ** ስለ እውነቱ ያለውን መልእክት ለመስማት እየጠበቃችሁ እንደሆነ አውቃለሁ። ይህም በዘመኑ ካሉ ታላላቅ ችግሮች አንዱ ነው። እናም የእኔ እዚህ መቆም እርግጠኛ እንደሆነ ሁሉ፡ ትክክለኛው መልስ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እንዳለ አምናለሁ፡ ስለዚህ ተመልሼ ለመምጣት ቃል የገባሁት ለዚህ ይመስለኛል።

18 እና እንዲህ፡ አስባለሁ፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ፡ እዚህ በጄፈርሰንቪል፡ በፋሲካ እሁድ ሌላ አገልግሎት እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ፡ እንዲህ እናደርጋለን… ለፀሐይ መውጫ አገልግሎት፡ ከዚያም የትንሳኤው እሁድ ላይ። ስለዚህ አስቀድመን እናሳውቀዋለን እና፡ ከተቻለ አዳራሹን፡ ወይም የሆነ ቦታ ለማግኘት እንሞክራለን፡ ለእሁድ፡ ምናልባትም ለቅዳሜ እና እሁድ እንመጣለን። ጊዜው ቅርብ ነውና፡ መብረር እና መመለስ አለብን… በመጀመሪያ፡ ባለኝ መርሐግብር፡ ማረጋገጥ አለብኝ፡ አንደኛው ጉዞዬ ወ—ወ—ወደ ካሊፎርኒያ ነው። ከዚያ በኋላ፡ በቀጥታ፡ ወ—ወደ አፍሪካ እጓዛለሁ። ስለዚህ ጠይቁን ጸልዩልንም።

19 አሁን፡ ዛሬ ማታ፡ በቅዱስ ሉቃስ ምዕራፍ 4 ላይ ወደሚገኘው፡ የእግዚአብሔር ቃል ክፍል ትኩረታችሁን እንድታደርጉ እፈልጋችኋለሁ። 4ኛው ምዕራፍ 16ኛው ቁጥር፡ በኢየሱስ ንግግር፡ ይጀምራል።

**… ዛሬ ይህ** ቃል **በጆሮአችሁ ተፈጸመ።**

20 አሁን ከዚያ በመነሳት፡ የእግዚአብሔር ቃል ምን ያህል አንቀሳቃሽ ኃይል እንደሆነ፡ አንድ ድምዳሜ ላይ መድረስ እንፈልጋለን! አሁን፡ እኛ ሁላችንም ሜካኒካል ነገሩን መገንዘብ እንችላለን፡ ይሁን እንጂ በትክክል ይሰራ ዘንድ አንቀሳቃሽ ኃይል ያስፈልጋል።

21 ሁላችንም የማሽን፡ የአውቶሞቢል ሜካኒክስ ምን እንደሆነ ማወቅ እንችላለን፡ ይሁን እንጂ ጎማዎቹ እንዲሽከረከሩ እንዲሰሩ እና እንዲንቀሳቀሱ የሚያደርግ ዳይናሚክ ይጠይቃል።

22 አሁን፡ ኢየሱስ ወዳደገበት—ወደ ናዝሬት፡ ተመልሶ መጥቶ ነበር። እዚህ በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ፡ እንዲህ ሲሉት እናገኛቸዋለን፡ “በቅፍርናሆም **እንዲህ-እና-እንዲያ** የመሳሰሉትን እንዳደረግህ ሰምተናል። እስኪ አሁን ደግሞ በገዛ አገርህ ስታደርግ እንይ።”

23 ኢየሱስም አላቸው፡ “ነብይ—በገዛ አገሩ በቀር ሳይከበር አይቀርም።” ያም፡ ማለት፡ ያደጋችሁበት ስፍራ፡ ሰዎች ሁሉ በሚያውቋችሁ ስፍራ ማለት ነው። በዚያም መ—መ—መጥፎ ስም ተሰጥቶት ነበር፡ በአንደኛ ደረጃ፡ ያለ ምድራዊ አባት በመወለዱ ነው። “ዲቃላ ልጅ” ይሉት ነበር፡ ይህ ማለት፡ ማርያም በይፋ ዮሴፍን ከማግባቷ በፊት፡ ነፍሰ ጡር እንደነበረ ነው፡ ይህን እንጂ፡ እንደዚያ አልነበረም፡ እንደዚያ እንዳልሆነ እኛ እናውቃለንና።

24 በዚህ መጻሕፍ ቅዱስ ቃል ላይ፡ አይኖቼ እንድጥልበት ያሰደረገኝ ነገር፡ በቅርቡ በፎኒክስ፡ አሪዞና ውስጥ የሆነ ነገር ነበር። ስብሰባው የሚያልቅበት፡

የአግለግሎት የመጨረሻ ቀን ነበር ቦታውም በአለም አቀፍ የሙሉ ወንጌል የቢዝነስ ሰዎች ኮንቬንሽን ላይ ነው።

25 እና በስብሰባው ውስጥም፡ የካቶሊክ ቢሾፕ የሆነ አንድ እንግዳ በመካከላችን ነበረ፡ እርሳቸውም—የ "የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የቻልዲያን ራይትስ ኦፍ ዚ ኣፖስቶሊክ ቸርች፥ እጅግ የተከበሩ ሬቨረንድ ጆን ኤስ. ስታንሊ ነበሩ፡ ኦ.ኤስ.ዲ.።" በካቶሊክ ቤተ ክርቲያን ውስጥ "የሜትሮፖሊታን ዩናይትድ ስቴትስ ሊቀ ጳጳስ፡" ናቸው። ይኸውና—አድራሻው እና ካርዱ **ይህ** ነው።

26 እርሱም ከክርስቲያን ነጋዴዎች ማሕበር አንድ ላይ እንግዳ ሆኖ በዚያ ነበር፡ ከዚያ ከአንድ ቀን ቀደም ሲል፡ አይቼው ነበር። እና ቅዳሜ ማታ ንግግር እያደርግኩ ሳለሁ፡ ይመስለኛል፡ ወይም ቅዳሜ ጠዋት ቁርስ ላይ ነው፡ እና... ንግግር እያደርግኩ ሳለሁ፡ እኔን ማየቱን ቀጠለ። እኔም "በርግጥም ያ ሰውዬ እኔ የምናገረው ነገር በሙሉ እየተቃወመ ነው፡" ብዬ አሰብኩ። እና፡ ይኸውላችሁ፡ እና ሰ—ስትመለከቱት፡ ጭንቅላቱን ወደ ላይ-እና-ወደ ታች ሲያደርግ ነበር፡ ነገር ግን በውስጡ ምን እየተፈጠረበት እንደነበረ ግን ማወቅ አልቻልኩም።

27 ስለዚህ እሁድ ከሰአት በኋላ፡ ንግግር ለማድረግ ስነሣ፡ **የምጥ ህመም** በሚል ርዕስ ላይ ለመናገር ተዘጋጅቼ ነበር፡ ኢየሱስ፡ እንዲህ በማለት እንደተናገረ፡ "ምጥ እንደሚይዛት ሴት፡" በምጥ ትታመማለችና። እኔም ከዚያ በመነሣት፡ **የምጥ ህመም፡** በሚል ርዕስ፡ ዓለም አሁን በምጥ ህመም እንዳለች ለመናገር፡ አስቤ ነበር። አዲሱ ይወለደ ዘንድ፡ አሮጌው ሊያልፍ ያስፈልጋልና፥ ይህም አንድ ዘር—አዲስ ሕይወት እንዲሰጥ፡ መበስበስ እንዳለበት አይነት ማለት ነው።

28 ህመሞቹም እንዲህ ነበሩ፡ ዓለም በምጥ ህመም ተመትታለችና! በአንደኛው የዓለም ጦርነት፡ በጣም ከባድ ህመም አሳለፈች፡ ምክንያቱም አለምን ሊያጠፋ የሚችል፡ መርዛማ ጋዝ፡ እና ልዩ ልዩ ነገሮች ታጥቀው ነበር። ከዚያም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት፡ ሌላ ከዚያ በከፋ ህመም፡ ተመታች፥ ደማሚቶች እና፡ ሌሎች አቶሚክ ቦምቦች ታጥቀው ነበር። ሌላ የምጥ ህመም መቋቋም አትችልም። ዛሬ ባሉት በእነዚህ ሚሳኤሎች እና ነገሮች፡ አንድ ተጨማሪ ጦርነት ቢመጣ ወደ ጠፈር ይሽኛታል፡ ምክንያቱ አሁን ትፈታለችና። እና አዲስ ምድር ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስም እንደምትመጣ ተናግሯልና።

29 በእያንዳንዱ ነቢይ መልእክት ስር፡ እስራኤል በምጥ ታማለች፡ ምክንያቱም እነዚህ ነቢያት ወደ ስፍራው ትዕይንት የሚመጡት ቤተ ክርስቲያን በሰነ መለኮት ምሁራን እና በቀሳውስት ተይዛ የድርጅት ቅርጽ በያዘች ቁጥር ነው። እና ነብያት **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** እያሉ ሲመጡ፡ አብያተ ክርስቲያናትን ያንቀጠቅጧቸዋል፡ የምጥ ህመምም ትያዛለች። በመጨረሻም፡ የወንጌልን ልጅ እስክትወልድ ድረስ በምጥ ህመም ትታመሳለች፡ ይህም ቃል ስጋ ሆነ ነው።

30 ስለዚህ ቤተክርስቲያን በእውነት ዛሬም፡ እንደገና፡ ስለ ልጅ ነጻ መውጣት፡ ስለ እግዚአብሔር ልጅ ዳግም መምጣት በእውነት በምጥ ላይ ነች። የሰነ መለኮት ምሁራኖቻችን ሁሉ፡ ስርዓቶቻችን በሙሉ፡ የሐይማኖት ተቋሞቻችን በሙሉ፡ ከበታቻችን ሆነው በሰብስዋል። ስለዚህ በምጥ ህመም ውስጥ ነን፡

ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ መልእክት በመጣ ቁጥር ቤተ ክርስቲያኒቱን ከበድ ወዳለው ህመም ያስገባታል፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ሙሽሪትን በመውለድ ትገላገላለች። ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ሙሽራው ያመጣል።

31 እና፡ ያኔ፡ ይህ ሰው እኔን በብርቱ እየተቃወመኝ ነው ብዬ አሰብኩ። ይህን መልእክት ለመናገር ስነሳ፡ ገጹን ለማግኘት፡ መጽሐፍ ቅዱሴን ገለጥኩት።

32 ያኔ ባለቤቴ ለገና፡ አዲስ መጽሐፍ ቅዱስ ሰጥታኝ ነበር። የድሮው መጽሐፍ ቅዱሴ አሥራ አምስት ዓመት ገደማ ሆኗታል፡ እና በጣም ተቀድዳ ነበር። ገጾቹ፡ በተከፈቱ ቁጥር፡ ይወዳድቁ ነበር። እና፡ ነገር ግን እያንዳንዱን ቅዱሳት መጻህፍት የት እንደሚገኙ ስለማውቅ፡ በዚያ መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ አጠናባት ነበር። ስለዚህ፡ አዲሱን ይዤ ወጣሁ፡ ምክንያቱ ሌላኛዋ እጅግ ስላረጀች፡ እሷን ይዤ ቤተ ክርስቲያን መሄድ አልቻልኩም ነበር።

33 ቃሉ በሚገኝበት ሰፍራ፡ በቅዱስ ዮሐንስ ውስጥ በከፈትኩ ጊዜ፡ ምዕራፍ 16ን ማንበብ ጀመርኩ፡ እኔ ስፈልገው የነበረ ቃል ግን እሱ አልነበረም። ስለዚህ “እንግዳ ነገር ነው!” በማለት አሰብኩ፡ እንደገና ከፈትኩ፥ አሁንም እሱ አልነበረም።

34 እና ወንድም ጃክ ሙር፡ ከሽሬቬፖርት፡ ሉዊዚያና፡ የቅርብ ጓደኛዬ፡ እዚያ ተቀምጦ ነበር። እርሱንም “ወንድም ጃክ፡ በቅዱስ ዮሐንስ 16 ላይ አይገኝም እንዴ፡” ብዬ ጠየቅኩት?

“አዎን፡” አለኝ።

35 እናም ይህ የካቶሊክ ቄስ ከመቶ የሚያህሉ ቀሳውስት፡ በመድረክ ላይ ከተቀመጡት ከመቀመጫው ተነሳ፥ ከነሙሉ ልብሶቹ እና ካባዎቹ እና መስቀሎቹ፡ እና የመሳሰሉትን ይዞ፡ ወደ እኔ መጣ እና ወደ እኔ ቀረበ። እና “ልጄ ሆይ፡ በርታ። እግዚአብሔር ለመጀመር ተዘጋጅቷል፡” አለኝ።

እኔም አሰብኩ፡ “እንዲህ ያለኝ አንድ የካቶሊክ ቢሾፕ ነውን? ”

“ከመጽሐፌ አንብበው፡” አለኝ።

36 ቃሉንም ከመጽሐፍ ቅዱሱ አነበብኩት፡ ለርዕስ የሚሆን ጽሑፍን ወሰጄ፡ ስብከቴን ሰበክሁ።

37 በኋላ ላይ፡ ከጨረስኩ በኋላ፡ ከሄድኩ በኋላ ተነሣና፡ እንዲህ አለ፡ “እነሆ አንድ ነገር ለመሆን ቀርቧል። ከዚያ በኋላ፡ ቤተ ክርስቲያን ከገባችበት ችግር መውጣት አለባት፡ ወይም ቤተክርስቲያን ከገባችበት አዘቅት ውስጥ እኛ መውጣት አለብን።” ስለዚህ፡ አንደኛው ወይም ሌላኛው።

38 እናም በዚያ ምሽት፡ ወደ ቱክሰን፡ ወደ ቤቴ በመንገድ ላይ ነበርኩ። ልጆቹ ሳንድዊች ፈልገው እያለቀሱ ነበር፡ እና ትንሽ መቆሚያ ላይ ሳንድዊች ለመግዛት ቆምን። ሚስቴም እንዲህ አለች፡ “ቢል፡ በዚያ ቆመህ መጽሐፍ ቅዱሱን ስታገላብጥ ሳይህ፡ እኔ በህይወቴ ሁሉ እንዲህ ፈርቼ አላውቅም።” “አንተንስ አላስጨነቀህምን፡” ብላ ጠየቀችኝ?

39 “አይ፡” አልኳት። “የሆነ ቦታ ውስጥ እንዳለ አውቅ ነበር። ችግሩ የህትመት ነው። ያቺ ገጽ ዘለዋታል፡” አልኳት።

40 እርሰዋም “ያን መጽሐፍ ቅዱስ፡ እኔ እንደገዛሁልህ ሳሰበው! የሰው ሁሉ አይኖች እኔን የሚያየኝ መሰሎኝ ነበር፡” አለችኝ።

41 እኔም “አይ፡ ምንም ማድረግ አይቻልም። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ የሕትመት ግድፈት አለበት፡” አልኳት። “ያቺ ገጽ በፍጹም አላካተቷትም፡” አልኳት።

42 ከዛ፡ እኔ ወደ ታች ገባሁ እና እንደገና ተመለከትኩት፡ መለየት በማይቻል መልኩ፥ 16 ኛው ምዕራፍ ክፍል፡ ማብቂያው፡ ቀሪ ክፍሉ የሚያበቃው በቀጣዩ ገጽ ላይ፡ በ17ኛው ምዕራፍ ላይ፡ ከሰር ወደ ላይ ሦስት ኢንች ከፍ ብሎ ነበር። እና፡ አዲስ መጽሐፍ ቅዱስ በመሆኑ፡ ሁለቱ ገጾች ፍጹም በአንድነት ተጣብቀው ነበር፡ እና ከ 16ኛው ይልቅ ከ 17ኛው ምዕራፍ እያነበብኩ ነበር። “እንግዲህ፡” “ምንም ችግር የለውም። በምክንያት ነው፡” አልኩኝ።

43 እና ማንኛውንም ድምጽ እንደምትሰሙት ሁሉ፡ አንድ ድምጽ ወደ እኔ መጣ፡ እና እንዲህ አለኝ፡ “ወዳደገበትም፡ ወደ ናዝሬት ገባ፥ እንደ ልማዱም፡ ወደ ምኩራብ ገባ። ካህኑም መጽሐፍትን ያነብ ዘንድ ሰጠው፡ ኢሳይያስ 61ን አነበበ። መጽሐፉንም ካነበበው በኋላ፡ ቁጭ አለ፥ መጽሐፍ ቅዱሱን፡ መጽሐፉን፡ ለካህኑ ሰጠውና ተቀመጠ። በጉባኤው የነበሩ ሰዎች ዓይኖቻቸው ሁሉ ትኩር ብለው ያዩት ነበር። ከአፉም የከበሩ ቃላት ወጡ። እርሱም ‘ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ፡’ አላቸው።”

“ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ።”

44 ቅዱስ ቃሉ እንዴት ፍጹም ነው! ይሄን በኢሳያስ 61፡1 እስከ 2 ካስተዋላችሁት፡ ጌታችን እያነበበ ከነበረበት ነው፡ ኢሳያስ 61፡1 እስከ 2። ኢሳይያስ 61 ላይ በ2ኛው ቁጥር መሃል ግን፡ ቆመ። እንዲህ ተብሎ በተጻፈበት ስፍራ፡ “የተወደደችውን የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ፡ የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፡” ያኔ ቆመ። ለምን? ፍርድን የሚያመጣ፡ ቀጣዩ ክፍል፡ ከዳግም ምጽአቱ ጋር እንጂ፡ በመጀመሪያ መምጣቱ የሚፈጸም ሰላይደለ ነው። እያችሁ፡ በዚያ የሚፈጸም አይደለም። ቅዱስ ቃላት በፍጹም አይሳሳቱም! ሁሌም ፍጹም ናቸው። ኢየሱስም መጽሐፉ በቆመበት ቆመ፡ ምክንያቱ በሱ ዘመን፡ ማለት፡ በመጀመሪያው ምጽአቱ ላይ ሊገለጥ የተገባው ያ ሰለነበረ ነው። የሁለተኛው ምጽአት በምድር ላይ ፍርድን ያመጣል፥ ያኔ ግን አልነበረም። “የተወደደች ዓመት ለመሰበክ” ነበር እንጂ።

45 መሲሑን በመድረክ ላይ ቆሞ፡ ለዛ ዘመን የተሰጠ የተሰፋ ቃል እራሱን ሲገልጥ አስተውሉ። እንዴት ድንቅ ነው፡ መሲሑ በቤተክርስቲያኒቱ ፊት ለፊት ቆመ! “የተወደደችውን ዓመት እሰብክ ዘንድ፡” ብሎ ሲናገር፡ እነዚያን ድንቅ ቃላት እየተመለከተ ነበር።

46 “የተወደደች ዓመት፡” ሁላችንም እንደምናውቀው፡ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች “የኢዮቤልዩ ዓመት፡” ናት። ማለት፡ ባሪያዎች እና እስረኞች ሁሉ፡ ተይዘው፡ ተወስደው፡ ዕዳ ለመክፈል፡ ወንድ ልጅ፥ ወይም ሴት ልጅ፡ ዕዳ መክፈል፡ ታስረው የነበሩ ሁሉ፡ [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—እርታዒ።] በባርነት ውስጥ ለነበሩ። ምንም ያህል ጊዜ በባርነት ውስጥ ቢቆዩ፡ ወይም ለምን ያህል ጊዜ መቆየት ነበረባቸው አይገደኝም፥ የኢዮቤልዩ ዓመት፡ ሲደርስ፡ ቀንደ መለከት ሲነፋ፡ ነፃ መሄድ ከፈለገ ሰው ሁሉ ነፃ መሆን ይችላል። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ።] ነጻ ናችሁ። ከእንግዲህ ባርያዎች አይደላችሁም።

47 ባርያ ሆኜ መኖር ይሻለኛል ካላችሁ ግን፡ ወደ ቤተ መቅደሱ ትወስዳላችሁ፡ በመቅደሱ ምሰሶ አጠገብ ትቆማላችሁ፡ ከዚያ በኋላ ወስፌ ይዘው ይመጡና ጆሮአችሁን ይበሳሉ፡ ከዚያ በኋላ ቀሪ ዘመናችሁ ሁሉ ባርያ ሆናችሁ ታገለግላላችሁ።

48 የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ግሩም ምሳሌው ነው! የተወደደች ዓመት፡ የኢዮቤልዩ ዘመን። ከተሰበከች፥ ማንም ሰው፡ ማንም ብትሆን፡ ምንም አይነት ቀለም ይኑርህ፡ የየትኛው ቤተ እምነት አባል ሁን፡ ምንም ያህል በኃጢአት የተያዘ ሰው ብትሆንም፡ ምንም አይነት ችግር ቢኖርብህም፥ የወንጌል መለከት ሲነፋ ከሰማህ በነፃነት መሄድ ትችላላችሁ። ነፃ ነህ!

49 መልእክቱን አልሰማም ብለህ ጆርባህን ሰጥተህ ቃሉን ለመሰማት ፍቃደኛ ካልሆንክ፡ አስተውል፡ ጆሮህ፡ በወስፌ ተበስተሃል። ይህ ማለት፡ በጸጋና በፍርድ መካከል ያለውን ድንበር አልፈሃልና፡ ዳግመኛ ወንጌልን አትሰማም፡ ማለት ነው። ከዚያ በኋላ ወደፊት መጓዝ አትችልም። ቀሪ ዘመንህ ሁሉ፡ የዚያ የገባህበት ስርዓት ባርያ ሆነህ ትኖራለህ፡ ይህም የተወደደችውን ዓመት ካልተቀበልካት ነው።

50 አሁን፡ ሌላኛው ክፍል፡ እንዳልኩት፡ መልሰ አያስፈለገውም፡ ምክንያቱም ይህ የሚመጣው መሲህ፡ ፍርድን የሚያመጣበት ጊዜ፡ አሁን ነው።

51 አሁን፡ እነዚያ ሰዎች ማንነቱ ማወቅ እንዴት ተሳናቸው? እንዴትስ ሳቱት? መታውቅ በሚችልበት መንገድ ግልጽ ሆኖ ሳለ፡ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? እንዴት እሱም ማየት ተሳናቸው? እሱ ራሱ...

52 እንዴት ያለ ቃል ነው! አሰቡት; “ይህ ቃል ዛሬ በፊታችሁ ተፈጸመ።” የተናገረው ማን ነበረ? የገዛ ቃሉ ተርጓሚ የሆነው፡ እግዚአብሔር ራሱ ነው። “ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ።” መሲሑ፡ ራሱ፡ በጉባኤው ፊት ቆሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል፡ ስለራሱ የሚናገረውን ክፍል አነበበ፡ እና “ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ፡” አላቸው፡ ቢሆንም አሁንም ማየት አልቻሉም።

53 ያ እንዴት ያለ አሳዛኝ ነገር ዮሆን፡ ግን ሆነ። ብዙ ጊዜ ሆኗል። እንዴት ሊሆን ቻለ? እንደሌሎቹ ዘመናት፡ የቃሉን የሰዎች ትርጓሜ በማመን እንደሆነ፡ የታወቀ ነው። ችግሩ ከዚያ ነው። በዚያ ዘመን የነበሩ፡ አማኞች-ተብዬዎቹ፡ ካህኑ ሰለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ትርጓሜ ይቀበሉ ነበር። ስለዚህ ከማናቸውም ስልጣን ወይም ከማህበራቸው አባል ያልነበረው፡ ኢየሱስ፡ ከድርጅታቸው ተወግዞ ነበር።

54 ስለዚህ፡ ከእነርሱ የተለየ ስለነበረ፡ ስለነበረ፡ እርሱን ከነሱ ጋር እንደ አንዱ አልቆጠሩትም። የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት እጅግ ልዩ ከመሆኑ የተነሳ ማንም ሰው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አይቶ ሊያጣው አይገባም ነበር፡ ምክንያቱ ስለሱ ስለተጻፈው ቃል ፍጹም የሆነ መታወቂያ የሚሆን ሰው ነበርና።

55 ማንኛውም ክርስቲያን የሚታወቀው በዚህ መንገድ ነው፡ ሕይወቱ ክርስቲያኖች ማድረግ ካለባቸውን ነገሮች ጋር ሲመሳሰል።

56 በፊታችሁ ቆሞ እንዲህ ሊላችሁ ይችላል፡ “ይህ ቃል ዛሬ በአይኖቻችሁ ፊት ተፈጸመ!” እንዴት ድንቅ ነው፡ እንዴት በግልፅ ነው፡ በዚህ ሁሉ ግን

ሰዎቹ አልተረዱትም። ለምን? ያኔ ያዳምጧቸው የነበሩትን አንዳንድ የካህናትን ሰርዓት ትርጓሜ ስለሚቀበሉ ነው።

57 ታሪክም ሁሌ ራሱን ይደግማል። ሌላ ደግሞ ቅዱሳን ቃላት ድርብ ትርጓሜ፡ እና ድርብ መገለጥ ስላላቸው ነው።

58 ለምሳሌ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ኢየሱስን በመጥቀስ፡ “ልጄን ከግብፅ ጠራሁት፡” ይላል። ይህ ጉዳይ ጥግ ጥጉን ካያችሁት፡ ሌላ ነገር ታያላችሁ፡ ያው ቃል፡ ስለ ያዕቆብም ይጠቅሳል። ኢየሱስ ታላቅ ልጁ ነውና። ያዕቆብ ከግብፅ የተጠራ ልጁ ነበር፡ ይህም የስኮፊልድ ማጣቀሻ እና ሌሎች ማጣቀሻዎች ሁሉ ያብራሩታል፡ ምክንያቱም እሱ የሚያመለክተው ቅዱስ ቃል ያ ነበር። ስለዚህ––ድርብ መልስ ነበረው፥ ያዕቆብ ስለመጠራቱ፡ እና ኢየሱስ ስለመጠራቱ መልስ ነበረው።

59 ዛሬም እንዲሁ ነው! ምክንያቱም እኛ ባለንበት ግርግር ውስጥ ስለሆንን፡ ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነት ማየት ተሰኗቸዋል፡ ምክንያቱም ብዙ ሰው-ሰራሽ የእግዚአብሄር ቃል ትርጓሜዎች ስላሉ ነው። እግዚአብሔር ቃሉን የሚተረጉምለት ማንም አይፈልግም። እሱ ራሱ የራሱ ተርጓሚ ነው።

60 እግዚአብሔር በመጀመሪያ፡ “ብርሃን ይሁን፡” አለ፡ ብርሃንም ሆነ። ያ የማንም ትርጓሜ አያስፈልገውም።

61 “ድንግል ትፀንሳለች፡” አለ፡ ጸነሰችም። ያ የማንም ትርጓሜ አያስፈልገውም።

62 ይህም… የእግዚአብሔር የቃሉን ትርጓሜ የሚሆነው ሊሆን ያለውን ሲገልጥ እና ሲረጋገጥ ነው። አተረጓጎሙ፡ ያለውን እንዲፈጸም በማድረግ ነው። የእግዚአብሔር አተረጓጎሙ እንዲህ ነው፡ ቃሉ እንዲፈጸም በማድረግ። የሚተረጉመው ለእናንተ ነው።

63 ለምሳሌ ብርሃን ባይኖር ኖሮ፡ እና “ብርሃን ይሁን፡” ካለ በኋላ፡ ብርሃን ከሆነ፡ ያ የማንም ትርጉም አያስፈልገውም።

64 እኛ ግን ሰው-ሰራሽ ሰርዓቶችን እንዲቀላቀሉበት እናደርጋለን፡ እና፡ እንዲህ ስታደርጉ፡ ከመሰመር––ታሰወጡታላችሁ። ከድሮ ጀምሮ እንዲህ ነው።

65 ምን አይነት አስገራሚ ነገር እንደሆነ እስከ አሁን ድረስ አሰበዋለሁ። እስቲ አስቡት፡ መሲሑን! እርሱን ማየት ለምን አቃታቸው? ምክንያቱም፡ እሱን ሊያውቁት የሚገባቸው መሪዎቻቸው፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን ጠንቅቀው የሚያውቁ፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሊረዱ የሚገባቸው መሪዎቻቸው፡ ይህን ሰው አቅልለውታል እንዲህ ብለውታል፡ “በመሰረቱ––ይህ ልጅ’ኮ፡ ከጋብቻ ውጪ የተወለደ ልጅ ነው። እኛ ልናምነውም አይገባንም።”

66 ከዓመታት በኋላ፡ እኛም አላመንነውም። በድንግልና-የተወለደ ልጅ ስለመሆኑ ለዚያ ዓላማ እንሞታለን።

67 አንድ ቀን ደግሞ እንዲህ ይሆናል፡ ያሕዌ ዛሬ ሲያደርግ የምናያቸው ነገሮች፡ በሚመጡ ዘመናት ያሉ ሰዎች፡ ከቀጠለ፡ እኛ ዛሬ ስለምንናገርላቸው ነገሮች ይሞታሉ። የአውሬው ምልክት ሲመጣ ይህ ማድረጋችሁ የማይቀር ይሆናል፡ ያኔ ይህ ወንጌል በዚህ መንገድ መሰበክ አይፈቀድላችሁምና። በአሁኑ ጊዜ ስለ ዓለም ቤተክርስቲያን ሥርዓት የተባለ፡ ታላቅ የአብያተ ክርስቲያናት

አንድነት ሲሰበሰብ፡ ስለዚህ ነገር፡ ያን ጊዜ ምስክርነታችሁን በገዛ ህይወታችሁ ታትሙታላችሁ።

68 አሁን ልታምኑት ይገባችኋል። እነዚያ የኮነኑት ካህናት፡ ቢነሱ ኖሮ፡ ባልኮነኑት ነበር። እናንተ፡ “ግን፡” እንዲህ ትላላችሁ፡ “እኔ እዚያ ብኖር ኖሮ **እንዲህ-እና-እንዲያ** ባላደረግኩ ነበር።” እንግዲህ፡ ያ የእናንተ ጊዜ አይደለም። ግን'ኮ፡ ጊዜአችሁ ይህ ነው፡ ዘመናችሁ ይህ ነው።

እናንተም “እንግዲህ፡ እሱ እዚህ ቢሆን ኖሮ፡” ትላላችሁ!

69 መጽሐፍ ቅዱስ ግን ስለሱ፡ “እሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እና ለዘላለም ያው ነው፡” ያው ነው፡ ስለዚህ አሁን እዚህ አለ። እሱ ግን፡ እዚህ አለ። ዓለም በሰለጠነች፡ ታላቅ በሆነች፡ በተማረች ቁጥር፡ እሱን ሊገድሉት ሊያጠፋት በማይችሉበት፡ በመንፈስ መልክ እዚህ አለ። አንዴ ሞቷል፥ እንደገና አይሞትም። እግዚአብሔር ስለ ኃጢአት በሥጋ ለመሞት፣ እንዲሞት ሥጋ መሆን ነበረበት። በዚህ ጊዜ ግን ፈጽሞ ሊሞት አይችልም፥ መንፈስ ቅዱስ ነው።

70 አሁን፡ በእሱ ላይ የነበረባቸውን እነዚያን ተቃውሞዎች ማሰቡ ራሱ! ሌላው ደግሞ፡ በማንኛውም ስልጣናቸው አይገባም። ስለዚህ፡ በዚህ ምክንያት፡ መጥፎ ሰው ያደርገዋል። በድርጅቶቻቸው—እና በክሃናት ስርዓታቸው፡ አይቀላቀልም፡ ከዚህጋር ምንም ግንኙነት አይኖረውም። ከዚህ ሁሉ፡ በተጨማሪ፡ የገነቡትን ለማፍረስ ሞከረ።

71 ወደ ቤተመቅደስ ገባ። የዋህ ሰው ነው እንላለን፥ ነበርም፡ ግን ብዙ ጊዜ የዋህነት ምን እንደሆነ እንስታለን።

72 ርህሩህ ሰው ነበር እንለዋለን፣ አንዳንዴ ግን ርህራሄ ምን እንደሆነ መረዳት ይሳነናል። የሰው ሀዘኔታ አይደለም፡ ርህራሄ ነው። **ርህራሄ** ግን፡ “የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ” ነው።

73 በቤተሳይዳ መጠመቂያ፡ በር አለፈ። በእዚያም ብዙ ሰዎች፡ ብዙዎች ተኝተው ነበር። ብዙዎች ሲባል የቁጥር ወሰን የለውም። በዚያ ግን፡ ብዙ አንካሶች፡ ዕውሮች፡ ሰላላዎች፡ ጉንድሾች ነበሩ፥ ሁልጊዜም፡ ለሰዎችም ይራራላቸዋል። እና አንካሳ፡ ዕዉር፡ ሰላላ፡ እና ጉንድሽ ወዳልነበረ ሰው ሄደ፥ ምናልባት የፕሮስቴት ችግር አጋጥሞት ሊሆን ይችላል፣ ምናልባት ትንሽ የተጎዳ አካል ነበረበት። ከበሽታው ጋር ለሠላሳ-ስምንት ዓመታት ኖረ። አያስቸግረውም፡ አይገድለውም። ምንጣፋ ላይ ተኝቶ ነበር። እርሱም አለው፡ “ትድን ዘንድ ትፈልጋለህን አለው? ”

74 ሰውዬውም አለው፡ “ውሃ ውስጥ የሚያኖረኝ ሰው የለኝም፡ እኔ እየመጣሁ ሳለ ግን፡ አንድ ሰው፡ ቀድሞኝ ይወርዳል።” አያችሁ፡ ይራመዳል፡ ያያል፡ መመላለስ ይችላል፡ ይሁን እንጂ የተጠቃ ሰው ነበር።

75 ኢየሱስም “ተነሳ። አልጋህን ተሸክመህ ወደ ቤትህ ሂድ፡” አለው። መጽሐፍም ይህን እንደ ተናገረ ታስታውሳላችሁና ስለዚህ፡ ኢየሱስ ተጠየቀ።

76 ምንም አይገርምም! ዛሬ እሱ ወደ ጀፈርሰንቪል ቢመጣና እንደዚያ አይነት ድርጊት ቢሰራ፡ ስለሱ መናገራቸው አይቀርም ነበር።

77 ነገር ግን፡ አስታውሱ፡ አንድ ነገር ለማድረግ መጣ፡ እሱም የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር። አሁን፡ ያ በቅዱስ ዮሐንስ 5፡19 ላይ ይገኛል፡ መልሱን ታገኛላችሁ።

እንዲህ ይላል፦ “እውነት፡ እውነት፡ እላችኋለሁ፥ ልጅ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም፥ አብ ሲያደርግ ያየውን ግን፡ ልጅ ደግሞ ያደርጋል።”

78 እንግዲህ፡ ይህ የሙሴ ትንቢት ማረጋገጫ እንደ ሆነ ሊያውቁ ይገባቸው ነበር፡ “እግዚአብሔር አምላክህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣል።”

79 አስተውላችኋል፡ ሰውዬውን ሲያየው፡ እንዲህ አለ... ኢየሱስ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ለብዙ ዓመታት እንደቆየ አወቀ። አያችሁ፡ ነብይ ስለነበረ፡ ሰውዬውን በዚያ ሁኔታ ሆኖ እየው፥ ወደዚያ ሄዶም ማለፊያውን—የሚያልፍበት መንገድ እየቀደደ በእነዚያ ሰዎች አልፎ ሄደና፡ በተሰበሰበው ህዝብ መኻል አልፎ፡ ግለሰቡን እስኪያገኘው ድረስ ተጓዘ።

80 አንካሶችን፡ ሰላላዎቹን፡ የታወሩትን፡ እና ጉንዱሾቹን አልፎአቸው ሄደ፡ ይሁን እንጂ ርኅራሄ የተሞላ ሰው ነበረ። ይሁን እንጂ፡ **ርኅራሄ** “የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ” ነው።

81 ስለዚህ፡ እንዳየነው፡ ከነሱ ጋር እንደማይተባበር ተረድተናል፡ በስልጣኖቻቸው መካከል ምንም ህብረት አልነበረውም፡ በተጨማሪም የተወገዘ ነበረ። ምንም ነገር አልነበረውም...

82 ከዚህም ሌላ፡ አንድ ቀን ወደ ቤተመቅደስ መጣና። ይህ ሰው ወደዚያ ገብቶ የእግዚአብሔርን ቤት እንደ ዛሬው እርኩሰት ተሞልቶ አየ። ይገዙ፡ ይሸጡ፡ ገንዘብ ይቀይሩ ነበር። የገንዘብ ጠረጴዛዎቹንም ገለበጠ። ገመድ ገመደና፡ ገንዘብ ለዋጮችንም ከቤተ መቅደስ ገርፎ አባረራቸው። በቁጣም ተመለከታቸው፡ እንዲህም አለ፡ “እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፡” ሃሌሉያ፡ “የአባቴ ቤት የጸሎት ቤት ነው፥ የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችኋት። እናንተም፡ በወጋችሁ፡ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ከንቱ አድርጋችኋል።”

83 ኦህ፡ እንደዚያ ያለ ጉባኤ በእርሱ ማመን ይችል ይሆን? አይችልም፡ ጌታዬ። በዘመኑ በነበረው እርኩሰት እና በማሕበረሰብ ጭቃ እጅግ-ተረግርገው ነበር፡ የኃያሉ አምላክ ኃይል ንዝረት እስከማይሰማቸው ድረስ በሐይማኖት ትብታብ ደንዝዘው ነበር። ምስኪኗ ሴት ልብሱን ነክታ መፈወስዋ የሚያስገርም አይደለም፡ የሰከረው ወታደሩ ግን ፊቱ ላይ ተፋበት እና ምንም አይነት ኃይል አልተሰማውም! አቀራረባችሁ ይወስነዋል። እይታችሁ ይወስነዋል። ወደ ቤተ ክርስቲያን ስትሄዱ፡ መሻታችሁ ይወስነዋል።

84 እንግዲህ እርሱን ቆሞ አይተነዋል። በዚህ ጥርጥር የለውም ችግሩ ግን ህዝቡ ማጠንቀቂያ፡ ማስጠንቀቂያ ሰምቷል... ካህኑ ሕዝቡን አስጠንቅቆ ነበር። “አሁን በሚቀጥለው ሰንበት፡ ወደዚህ ይመጣል፡ እርሱ ሲመጣ፡ እንዳትሰሙት። ሄዳችሁ ቁጭ ማለት፡ ትችላላችሁ፡ ይሁን እንጂ ለሚለው ነገር ትኩረት አትሰጡ፡ ምክንያቱ እሱ የቡድናችን አባል አይደለም። የተወገዘ ነውና። የህብረት መታወቂያ የለውም። የድርጅት ወረቀት እንኳን የለውም። እንደዚህ አይነት ነገር የለውም።”

“እሱ ማን ነው? ”

85 “ከአንድ የአናጢ ቤተሰብ፡ በሕገወጥ ልደት የተወለደ፡ ምናምንቴ ልጅ ነው፡ ከመጋባታቸው በፊት እናቱ እርሱን አረገዘች፡ እና ነገሩን መለኮታዊ በሆነ ነገር ለመደበቅ እየሞከሩ ነው።

86 “መሲሑ ሲመጣ፡ በሰማይ ኮሪደሮች እንደሚወርድ፡ እና ወደ ሊቀ ካህናችን ፊት ቀርቦ “ቀያፋ ሆይ፡ እነሆ መጥቻለሁ፡’ እንደሚለው እናውቃለን።” ይህን እንጂ በዚያ መንገድ እንዳልመጣ እኛ እናውቃለን፡ ምክንያቱ በቃሉ ላይ እንደዚያ እንደሚሆን የተጻፈ ቃል የለም። ያንን እንዲያምኑ ያደረጋቸው ሰው-ሰራሽ ወግ ነው።

87 ቃሉ የሚናገረው እሱ በመጣበት አመጣጥ እንደሚመጣ ነበር። በዚያም ቆሞ፡ ቃሉን እያነበበ፡ እንዲህ አላቸው፡ “ይህ ቃል ዛሬ በዓይኖቻችሁ ፊት ተፈጸመ።” እና አሁንም ልክ እንደሌሎች ዘመናት፡ እርሱን ማየት ወይም እሱን ማወቅ ተሳናቸው።

88 ኖህ ወደ መርከብ በገባበት እና በሩ በተዘጋበት ቀን፡ ተመሳሳይ ነገር ተናግሯቸው ይሆናል። ሙሴም በታቦቱ እናት ላይ የነበረውን መሰኮት ከፍቶ፡ ውጪ ወደ ነበረው ጉባኤ አይቶ ይሆናል... አስታውሱ፡ በሩን የዘጋው እግዚአብሔር ነበረ። ስለዚህ እንዲህ ብሏቸው ይሆናል፡ “ይህ ቃል ዛሬ በአይኖቻችሁ ፊት ተፈጸመ፡” ያኔ ግን እጅግ ረፍደባቸው ነበር። ወደ ሠራው መርከብ ሊያስገባቸው እየሞከረ፡ አንድ መቶ ሀያ ዓመት ሰበከ፡ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲህ ይላሉ ብሎ እየነገራቸው፡ “የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ እነሆ ዝናብ ይዘንባል አላቸው፡” ይሁን እንጂ ረጅም ጊዜ ጠበቁ። ኖህ ግን በቀላሉ እንዲህ ሊል ቻለ፡ “ዛሬ፡ በዚህ ቀን፡ ቃሉ ተፈጽመዋል።”

89 ሙሴም፡ የእሳት ዓምድ በሲና ተራራ ላይ በወረደበት ቀንና ምስክሩን በመሰከረበት ቀን፡ ሙሴም “ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ፡” ሳይላቸው አይቀርም።

90 ሙሴ፡ እንደምታውቁት፡ በእግዚአብሔር የተጠራ፡ ነብይ ነበር። እርሱ የተጠራ በመሆኑ፡ ነብይ በመሆኑም፡ መለኮታዊ ልምምዶች ሊኖሩት ይገባል። ነቢይ ይሆን ዘንድ፡ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት መገናኘት እና ከእርሱ ጋር መነጋገር ነበረበት። እና ሌላ ነገር ደግሞ፡ የተናገረው ነገር መፈጸም ነበረበት፡ ካልሆነ ማንም አያምነውም።

91 ስለዚህ ማንም ሰው በሆነ መንገድ በምደረ በዳ ከእግዚአብሔር ጋር፡ ፊት ለፊት ካልተነጋገረ በቀር፡ ከእግዚአብሔር ጋር፡ እሱ ራሱ ካልተገናኘ ነብይ ነኝ ማለት አይችልም። በዓለም ላይ ያሉ አምላክ የለሽ ሰዎች ከእርሱ ሊለዩት ዘንድ ስለሱ ሊያብራሩለት አይቻላቸውም፡ እሱ ራሱ በዚያ ነበረ፡ ሲፈጸምም ራሱ ያውቀዋልና። እያንዳንዱ ክርስቲያንም ክርስቲያን ስለመሆኑ አንድ ነገር ከመናገሩ በፊት ይህን ልምምድ ሊኖረው ይገባል። የግልህ ልምምድ!

92 የወንድሜን ልጅ፡ ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ አንድ ትንሽ ካቶሊክ ልጅ አነጋገርኩት፡ እንዲህ አለ፡ “አጎቴ ቢል፡ የሆነ ነገር አገኛለሁ ብዬ በማሰብ፡ ከአንዱ አምድ፡ ወደ ሌላ ምሰሶ ዞርኩኝ።” ይህ ሰብሰባ ከመጀመሩ በፊት፡ ከማታ ወደ ማታ፡ ሲያለቅስ ቆይቷል። እና ሲመሽ፡ ወደዚህ ሲመጣና፡ ወደ መሰውያው ሮጦ ሲመጣ ህልም ያያል፡ እየተሰበከ ሳለ፡ መሳሳቱን እየተናዘዘ ኀሰሃ ሲገባ ያያል።

93 እኔም አልኩት፡ “ሜልቪን፡ የትም ብትሄድ፡ ምንም ያህሉ አብያተ ክርስቲያናት ብትቀላቀል፡ ምንም ያህል ‘ሰላም ለኪ ማርያም፡’ ብትልም፡ ወይም ምንም ያህል በረከት ከሰው ቢመርቁህ፡ ከእግዚአብሔር መንፈስ ዳግመኛ መወለድ አለብህ። የሰውን ልብ የሚያረካው ብቸኛው ነገር እሱ ነው።”

94 ማለት፡ ዛሬም፡ ዳግም ልደትን የሚተካ ነገር እንደፈለሰፉ፡ እውቃለሁ፡ ከሰባኪው ጋር እጅ በመጨባበጥ እና ስምህን በቤተክርስቲያን መዝገብ በማስፈር። ይሁን እንጂ፡ ወዳጆች ሆይ፡ ይህ ዶግማ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት አይደለም። ቢሆን ኖሮ፡ የሐዋርያት ሥራ፡ በ 2ኛው ምዕራፍ፡ እንዲህ በተነበበ ነበር፡ "የበዓለ አምሳ ቀን በደረሰ ጊዜ፡ ፓስተሩ ወጥቶ የህዝቡን እጅ ጨበጠ።"

95 የሚለው ግን፡ "የበዓለ አምሳ ቀን በደረሰ ጊዜ፡" በቤተክርስቲያን ምረቃት ቀን ላይ፡ "እንደ ዓውሎ ነፋስም ያለ ድምፅ ከሰማይ መጣ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው።" መንፈስ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚመጣው እንደዚህ ነው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በእያንዳንዱ ጊዜ የሚመጣው እንደዚህ ነው። እርሱ አምላክ ነውና፡ አይለወጥምም። አሁን፡ ሰዎች ይስናከሉበታል።

"ያ'ማ ለሌላ ዘመን ነው፡" ይላሉ።

96 እንግዲህ፡ እሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለም ድረስ ያው ነው። ቤተክርስቲያኑ መንፈስ ቅዱስን በተቀበለችበት ጊዜ ሁሉ፡ እሱ በመጀመሪያው ጊዜ በመጣበት መንገድ ነው፡ በተመሳሳይ ማዘዣ፡ የሐዋርያት ሥራ 2:38፣ ፈጽሞ አልተለወጠም፡ ፈጽሞ አይለወጥም።

97 ለበሽታ እንደሚታዘዝ የሀኪም ማዘዣ። ሐኪሙ፡ ለበሽታው የመድሐኒት ማዘዣ ይጽፋልና። ከዚያም ወደ አንድ አስመሣይ ባለመድኃኒት ይወስዱታል፡ እሱም ብዙ ጸረ መርዛማ መድኃኒት ያሽክማችኋል፡ ኃይል አልባ ስለሆነ አይጠቅማችሁም፥ እርሱም መርዙን ካበዛባችሁ፡ ይገድላችኋል። በሐኪሙ ማዘዣ መሠረት ብቻ መፃፍ አለበት።

98 እና መንፈስ ቅዱስን የምንቀበልበት የዶክተሩ ማዘዣም በጴንጤቆስጤ ቀን፡ በዶክተር ስምዖን ጴጥሮስ የተሰጠን ነው። "የመድሃኒት ማዘዣ እሰጣችኋለሁ። ንሰሓ ግቡ፡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ፡ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ። የመድኃኒት ማዘዣውም በሩቅ ላሉትና፡ ጌታ አምላካችንም ለሚጠራቸው ሁሉ ነውና።" ዘላለማዊው የመድኃኒት ማዘዣ!

99 ሙሴ ይህን ልምምድ አገኘውና። ወደ አገሩ ወርዶ ለሕዝቡ እንዲህ ይላቸው ጀመር፡ "የእሳቱን አምድ አገኘኝ። በሚቃጠል ቁጥቋጦ ስር ነበር። እርሱም 'እኔ እኔ ነኝ፡ ብለህ ንገራቸው አለኝ። ውረድ፥ እኔም ከአንተ ጋር እሆናለሁ። በትሩን በእጅህ ውሰድ በግብፅ ላይ አንሣው፥ የጠየቅከው ሁሉ ይፈጸማል።'"

ምናልባት፡ አንዱ ካህን "ከንቱነት፡" ብሎት ይሆናል!

100 ነገር ግን የዚህን እውነተኛ እውነታ፡ መፈጸሙን፡ ሲመለከቱ፡ ከዚያ በኋላ መቋቋም አልቻሉም። ከእግዚአብሔር እንደተላከ አውቀውት ነበርና።

101 ከዚያም፡ ሙሴ ያንን አይቻለሁ ካለ፡ እና እውነት ነው ብሎ ከመሰከረ፡ ይህ እውነት ከሆነ፡ እግዚአብሔርም በዚያን ሰው ቃል ዘንድ፡ በዚያ እውነት መኖሩ፡ እራሱን ከሱ ጋር በመለየት እና በማረጋገጥ ማሳየት ይጠበቅበታል። በትክክል።

102 ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያ ቀን ቆሞ፡ "ይህ ቃል ዛሬ በፊታችሁ ተፈጸመ፡" ብሎ ካነበበ፡ እግዚአብሔር ያንን ቃል እንዲፈጸም የማድረግ ግዴታ አለበት።

103 ዛሬ ማታ እዚህ ቆመን፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው፡” እንላለን። ቃሉ ስለሆነ፡ እግዚአብሔር ይህ እውነት መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት። አሁን፡ ምን ይጠይቃል? ይህን ለማመን፡ እምነት ይጠይቃል። እውነት ስለመሆኑ፡ ቃሉን ለማመንም፡ እምነት ይጠይቃል።

104 ሙሴ ልጆች ሁሉ እና እርሱን የተከተሉት በሙሉ ካሰወጣቸው በኋላ፡ የሆነውንን ነገር ልብ በሉ። ያልተከተሉት በግብፅ ቀሩ። ሙሴን የተከተሉት ግን፡ ከቀይ ባሕር ወጥተው ወደ ምድረ በዳ በወጡ ጊዜ፡ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ወረደ። ያ የእሳቱ ዓምድ ተራራውን ሁሉ በእሳት አቃጠለ፡ ድምፅም ከዚያ ወጣ፥ እግዚአብሔርም አሥሩን ትእዛዛት ሰጠ።

105 ሙሴ በሕዝቡ ፊት ወጥቶ ወደዚያ ሄዶ፡ እንዲህ ሊላቸው ይችላል፡ “የሱ ነብይ እንደመሆኔ፡ ይህ ቃል እንደነገርኳችሁ፡ ዛሬ በዚህ ቀን ተፈጸመ። እግዚአብሔር በዚያ በሚነድ ቁጥቋጦ ውስጥ፡ በእሳት ዓምድ ውስጥ፡ እንዳገኘኝ ነግሬአችኋለሁ፡ እንዲህም አለኝ፡ ‘እንዲህ ይሆናል... ይህ ምልክት ይሆናል። ሰዎችን እንደገና ወደዚህ ቦታ ትመልሳቸዋለህ።’ በዚያም በነገርኳችሁ፡ በእሳት ዓምድ ውስጥ፡ እግዚአብሔር በዚያ በተራራው ላይ ወርዷል። ይህ ትንቢት ዛሬ ተፈጸመ። እዚህ ላይ የተናገርኩት ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ነው።”

106 እግዚአብሔር እንደዚ አይነት ሰዎች አብዝቶ ይሰጠን፡ ሐቀኛ እና ቅን ናቸው፡ እውነቱን ይናገራሉ፡ ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ ቃሉ አሁንም እውነት መሆኑን ማረጋገጥ ይችላል! እሱ ትናንትና፡ እና ለዘላለም ያው ነው። ለምን አያደርገውም? እንደሚያደርገው ቃል ገብቷል።

107 ኢያሱም ወደ ቃዴስ-በርኔ በገባ ቀን፡ እንዲሁ ተናግሮ ሊሆን ይችላል፡ በምድረ በዳ ውስጥ ተጉዘው በዚያ ደርሰው ነበርና። ምድሪቱን እግዚአብሔር የተናገራቸው ዓይነት ምድር መሆኗን ተጠራጥረው ነበርና። እግዚአብሔር ግን መልካም ምድር፡ ወተትና ማር የምታፈስስ መሆኗን ነገራቸው። ኢያሱና ካሌብም ከጠፉቱ ከሌሎቹ አሥሩ፡ ተለይተው ያመኑ ሁለቱ ብቻ ነበሩ። ተመልሰው በመጡ ጊዜ፡ ማስረጃ ይዘው ነበር፥ ሁለት ብርቱዎች ብቻ የሚሸከሙት የወይን ዘለላ ይዘው መጡ።

108 ኢያሱና ካሌብ እዚያው ቆመው እንዲህ ማለት ይችላሉ፡ “ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ። መልካም ምድር ስለመሆኗ ማስረጃው ይኸው ነው።” አዎን። ለምን? “ጥሩ ምድር ስለመሆኗ ምስክሩ ይህ ነው። በግብፅ ውስጥ እንደዚህ ያሉ ነገሮችን ከየት ታገኛላችሁ? እንደዚህ ያሉ ቦታዎች አልነበሩም። ዛሬ ግን ይህ ቃል ተፈጸመ።”

109 ትንቢት በሚናገር ጊዜም፡ እንዲሁ፡ ሊናገር ይችል ነበር የኢያሪኮ ግንብ በቀን ሰባት ጊዜ፡ ሰባት ቀን፡ ሰባት ጊዜ ከዞሩ በኋላ ይወድቃል ባለ ጊዜም መናገር ይችል ነበር። እና የመጨረሻ ዙር በዞሩ ጊዜ፡ ግንቡ ፈረሰ። ኢያሱም ቆሞ እንዲህ ማለት ይችል ነበር፡ “በዚህ ቀን፡ የሰራዊት አለቃ ይህ ይሆናል ብሎ ከሳምንታት በፊት እንደነገረኝ፡ ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ።” ግድግዳዎቹ መሬት ላይ፡ ተዘርግተው ነበርና። “ኑ፡ የእኛ ናትና። እንውሰዳት። ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ።”

110 የእግዚአብሔር ሰዎች፡ ለትክክለኛው ነገር መቆማቸው እንዴት ድንቅ ነው!

111 እስራኤል፡ በወንዙ አጠገብ፡ ምድሪቱን በወረሱ ጊዜ፡ ተሻገሩ። እንዴት ሊያደርጉት ይችላሉ? በሚያዝያ ወር ነበረ። ጎርፉ በኃይል ይወርዳል ምክንያቱ በይሁዳ ተራሮች፡ በረዶዎች ይቀልጣሉ። ኧረ፡ ዮርዳኖስ ከማንም ጊዜ በላይ ሞልቶ በሚፈስበት ወቅት፡ በሚያዝያ ወር ላይ፡ እግዚአብሄር ህዝቡን ወደዚያ ማምጣት የፈለገ ይመስላል፡ ምን አይነት ሞስኪን ጄነራል ነው። አንዳንዴ...

112 እዚህ ላይ ላቆ እችላለሁ፡ ጊዜ ቢኖረኝ፡ አንዳች ምክር ጣል አደርጋለሁ። አንዳንድ ጊዜ ከካንሰር ጋር ቁጭ ልትሉ፡ ወይም ከሕመማችሁ ጋር እዚያ ቁጭ ልትሉ ትችላላችሁ፥ እናንተም እንዲህ ብላችሁ ታስባላችሁ፡ “ለምን ግን፡ እኔ፡ ክርስቲያን ሆኜ፡ ለምን እንዲህ ይሆንብኛል? እኔ’ኮ ክርስቲያን ነኝ፡ ለምን እንዲህ እቀመጣለሁ? ” አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር፡ ዙርያችሁን ወይም ሌላ ነገር ማየት እስከማትችሉ ድረስ፡ እጅግ ያሰጨልመዋል፡ ከዚያም መጥቶ በእርሱ መንገድን ያደርግላችኋል፡ ይህም እናንተ ደግሞ “አደርጋለሁ ብሎ እንደተናገረ፡ ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ፡” እንድትሉ ነው።

113 የዕብራውያን ልጆች ወደ እቶን እንዲገቡ ፈቀደ። እነርሱም እንዲህ አሉ፡ “አምላካችን ከዚህ በምድጃ ውስጥ ካለው እሳት ሊያድነን ይችላል። ግን፡ ባያድነንም፡ ለምስልህ አንሰግድም።” ከዚያ ሲወጡ፡ የእቶኑ ሽታ እንኳ በላያቸው ላይ... ማለት፡ በላያቸው ላይ፡ የእቶኑ ሽታ አልነበረም፥ ስለዚህ “ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ፡” ማለት ይችሉ ነበር።

114 ዳንኤል ከአንበሶች ጉድጓድ በመጣ ጊዜም፡ ተመሳሳይ ነገር መናገር ይችል ነበር።

115 መጥምቁ ዮሐንስ። ከአራት መቶ ዓመታት የሐይማኖቶች ትምህርት በኋላ፣ ያን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በዚያ ምስቅልቅል ውስጥ መግባቷም ምንም አያስደንቅም! ከዚያ ከምድረበዳ ወጥቶ፡ በዮርዳኖስ በታየ ጊዜ፡ ያን ጊዜ እንዳደረገው፡ በዳርቻዎቹ ላይ ቆሞ፡ “ይህ ቃል፡ ኢሳያስ 40፡ ዛሬ ተፈጸመ፡” ማለት ይችል ነበር።

116 ስለዚህ እሁን እዚህ ላይ ቆም አድርጌ ያ ሽማግሌ ካግን የተናገረኝን ብነግራችሁስ! እንዲህ አለኝ፡ “ልጄ ሆይ፡ ያንን መልእክት ገና አልጨረስከውም።”

እኔም “ዝም ብለህ ጠብቅ፡” አልኩት።

“ጴንጤዎቹ ይሄን አላዩትም ማለትህ ነው፡” ብሎ ጠየቀኝ?

እኔም “አላዩትም፡” አልኩት።

117 “ገባኝ፡” አለ። ደግሞ’ኮ፡ የካቶሊክ ካህን ነው! ኧሃ-ሃህ። “ለምን አልቀጠልክም፡” ብሎ ጠየቀኝ?

እኔም “ዝም ብለህ ጠብቅ፡” አልኩት።

እሱም “ክብር ለእግዚአብሔር! ገብቶኛል፡” አለኝ።

118 በዚያን ጊዜም መንፈስ ቅዱስ፡ በዚያ በጉባኤው ላይ ተቀምጣ ወደነበረች እህቱ ላይ ወረደ። ተነስታም፡ በማይታወቁ ልሳኖች ተናገረች፡ ትርጉሙም እኔና ካህኑ በመድረኩ ላይ እየተነጋገርንበት የነበረውን፡ በትክክል ሰጠች። መላው ቤተ ክርስቲያን፡ ሰፍራው ሁሉ፡ በሰዎች ድምጽ ተጥለቀለቀ። ባለፈው ሳምንት፡ ወይም ከባለፈው ሳምንት በፊት ወደ ነበረው ወደ ኦራል ሮበርትስ ኮንቬንሽን

ተዛምቶ፡ የኮንቬንሽኑ ታላቅ ዜና ሆኖ ስነበተ። እንዴት ያ ቄስ... በመንፈስ ቅዱስ ስር ሆና፡ በአንዲት ሴት በኩል ገለጠው፡ እህቱ ትመስለኛለች፡ በዚያ በመድረኩ ሲፈጸም የነበረው ነገር፡ እና ደብቀን ስንነጋገርበት የነበረውን ጉዳይ ገለጠው።

119 አሁን የምንኖርባት ሰዓት፡ ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ። በዛሬ ቀን የምሽት መብራቶች መጥተዋል፡ እኛ ግን ማየት ተሰኖናል። አስተውሉ።

120 ዮሐንስ እንዲህ አለ፡ "ዛሬ እኔ 'በነቢዩ ኢሳይያስ የጌታን መንገድ አዘጋጁ፡' እንደተባለ፡ 'በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ ነኝ።'"

121 እነርሱ አልገባቸውም። እንዲህ አሉት፡ "ኦህ፡ አንተ ኢየሱስ ነህን... ማለቴ—አንተ ክርስቶስ ነህን፡" አሉት።

122 "እኔ ክርስቶስ አይደለሁም፡" አለ። እንዲህ አለ፡ "የእግሩን ጫማ ለመፍታት እንኳ ብቁ አይደለሁም። ነገር ግን፡" እንዲህ አለ፡ "እርሱ በመካከላችሁ፡ ቆሟል አለ፡" ምክንያቱም እርሱ እዚያው እንደነበረ እርግጠኛ ነበርና። እግዚአብሔር መሲሑን እንዲያስተዋውቅ ስለነገረው፡ በዘመኑ ይሆናል።

123 አንድ ቀን አንድ ወጣት ሰው በዚያ በኩል እየተራመደ መጣ፡ እርሱም በእርሱ እናት ላይ ብርሃን፡ ምልክት አየ። በታላቅ ድምጽም "እነሆ፡ የእግዚአብሔር በግ! ይህ ቃል ዛሬ በፊታችሁ ተፈጸመ፡" አላቸው። በትክክል።

124 በጴንጠቆስጤ ቀን፡ ጴጥሮስ ተነሥቶ ከኢዮኤል መጽሐፍ 2፡38 ላይ፡ ጠቀሰላቸው። ሰዎቹም፡ ሁሉ፡ እየሳቁባቸው ሳለ። በገዛ ቋንቋቸው መናገር አቃታቸው። ሌላ ነገር መናገር ጀመሩ። መጽሐፍ ቅዱስ፡ "የተከፋፈሉ ልሳኖች" ይለዋል። **የተከፋፈለ** ማለት "የተለያየ" ልሳን ማለት ነው፡ ምንም ሳይናገሩ፡ ዝምብሎ መዘባረቅ። እንደ ሰካራም ሰዎች መንገዳገድ!

125 ሁሉም፡ "መልካም፡ እነዚህ ሰዎች ሰክረዋል። ሴቶችንና ወንዶች፡ እንዴት እንደሚሆኑ፡ ተመልከቷቸው። ሥርዓት አልባ ናቸው" አሉ፡ በዘመኑ የነበሩ የሃይማኖት ቡድኖች።

126 በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ በመካከላቸው ቆሞ፡ እንዲህ አለ፡ "ወንድሞች ሆይ፡ በኢየሩሳሌም የምትኖሩና፡ በይሁዳ የምትኖሩ ሁሉ፡ እነዚህ ሰዎች እንደምትገምቱት፡ የሰከሩ አይደሉም፡ ምክንያቱም ገና ቀኑ ሦስተኛ ሰዓት ነው። ነገር ግን ይህ በነቢዩ ኢዩኤል የተባለው ነው፡ 'በመጨረሻው ቀናት እንዲህ ይሆናል፡ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ።' ዛሬ ይህ መጽሐፍ ተፈጸመ።" በእርግጠኝነት።

127 ሉተር በትክክለኛው ዘመን ነበር። ዌስሊ በትክክለኛው ዘመን ነበር። ጴንጤቆስጤ በትክክለኛው ዘመን ነበር። ምንም ነገር ከሰርዓቱ ውጭ አልነበረም።

128 አሁን የምንኖርበትን ዘመንና ሰአት ለዘመናችን ከተገባልን ቃል ጋር፡ እንድትመለከቱት እጠይቃችኋለሁ። በሌላ ዘመን ሰዎች፡ "ዛሬ ይህ መጽሐፍ፡" "ዛሬ ይህ መጽሐፍ፡" ብለው ቢናገሩ፡ ታዲያ ስለ ዘመናችን ቃል ምን ማለት ይቻላል? ለዚህ ዘመን ምን ተስፋ ተሰጥቶናል? የምንገኘው የት ነው? የሳይንስ ሰዓት፡ እኩለ ሌሊት ሦስት ደቂቃ ሲቀረው፡ የምንኖረው፡ በየትኛው ሰዓት ላይ ነው? ዓለም ተጨንቃለች። ቤተክርስቲያን በብሉሹነት አልጋ ላይ ትገኛለች። የት

እንደቆሙ ማንም አያውቅም። በዛሬው ጊዜ ስንት ሰዓት ነው? ስለ ዘመናችን ቃልስ? የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ፡ ወይም፡ የዛሬው የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ!

129 ዓለም፡ ፖለቲካ፡ ዓለም አቀፋዊ ሥርዓቶቻችን፡ ሊበስብስ ከሚችለው በላይ የበሰበሰ ነው። ፖለቲከኛ አይደለሁም። እኔ ክርስቲያን ነኝ። ስለ ፖለቲካ ግን፡ የማወራበት ምክንያት የለኝም፡ በሁለቱም በኩል ግን የበሰበሱ ናቸው ማለት እፈልጋለሁ።

130 እኔ አንድ ጊዜ ድምፅ ሰጥቻለሁ፡ ይህም ለክርስቶስ ነበር፣ ማሸነፍ አለብኝ። ዲያቢሎስ በተቃራኒው ድምጹን ሰጠ፡ ክርስቶስ ግን ድምጹን ለእኔ ሰጠ፡ ድምፄን በየትኛው መንገድ እንደሰጠሁ ይወሰናል። በእሱ ላይ መጣል በመቻሌ ደስ ብሎኛል፣ ዓለም የፈለገውን ይናገር። ትናንትም፡ ዛሬም ለዘላለምም፡ ያው አምላክ እንደሆነ አሁንም አምናለሁ። ይህን ያረጋግጣል። በእርግጥም ያረጋግጣል። በእርግጠኝነት።

የወንጀል መብዛት፡ የወጣቶች ወንጀል!

131 ብሔራችንን ተመልከቱ፡ በአንድ ወቅት የምድር አበባ የነበረውን፡ በነጻነት አዋጅ ላይ የ—የተመሰረተውን… ታላቁን ዴሞክራሲያችንን ተመልከቱ፡ የነፃነት አዋጅ የተፈረመበት፡ ታላቅ ዴሞክራሲ ነበረን፡ ታላላቅ ቅድመ አያቶቻችንና፡ ያደረጉት ነገር፡ ታላቅ ሀገር ነበረን።

132 አሁን ግን እየበሰበሰች፡ እየፈረሰች፡ እየተንቀጠቀጠችና፡ እየጠፋች ነው። ወደ ውጪ የሚላክ ገንዘብ ለማግኘት፡ ከሰዎች ግብር ለመውሰድ መሞከር፡ ከጠላቶቻቸው ጋር ወዳጅነትን ለመግዛት ይሞክራሉ፣ ነገር ግን ፊታችን ላይ መልሰው እየጣሉት ነው። አንደኛ የዓለም ጦርነት፡ ሁለተኛ የዓለም ጦርነት፡ አሁንም ወደ ሦስተኛው እየተጓዙ ነው። እርግጥ ነው። ፖለቲካ የበሰበሰ፡ የተበላሸ፡ እስከመጨረሻው የበሰበሰ ነው። በማቴዎስ ምዕራፍ 24 ላይ እንደተገለጸው፡ “ሕዝብ በሕዝብ ላይ፡ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣል።” እነዚህ ሁሉ ነገሮች ይፈጸሙ ነበር። አሁን ይህንን እናስብበት። መልካም።

133 ሌላው ደግሞ፡ የሳይንሳዊ ምርምር መጨመሩን ልብ በሉ። አሁን፡ በአንድ ወቅት፡ እ… አያቴ፡ ሴት አያቴን ለማየት በከብት ጋሪ ይጓዝ ነበር። በአሁን ወቅት በጄት አውሮፕላን ነው፡ አልፎ ተርፎም ወደ አየር፡ ወደ ውጪ ጠፈር የሚጓዝ አውሮፕላን ነው። ግሩም ነው… ማን፡ ይህን የተናገረው ማን ነበረ? ዳንኤል 12፡ 4፡ እንዲህ ይላል፡ “በመጨረሻው ዘመን እውቀት ይበዛል።” የምንኖርበትን ወቅት እንየው። አሁን የ—የዓለምን ሁኔታ፡ የሳይንስን ሁኔታ ልብ በሉ።

134 እንደገና፡ በዛሬው ጊዜ፡ ትምህርት ሰርዓታችችንን ልብ በሉ። አሁን ይህንን ለማስተባበል አትሞክሩ። ጋዜጣ አንብብያለው፡ ወጣት ተማሪዎች እርስ በ-… በእርስ ወሲባዊ ግንኙነት እንዲፈጽሙ፡ በዓለም ውስጥ መገናኘት ይችሉ እንደሆነ ለማየት፡ በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ ወሲብ ያስተምራሉ። አዎ፡ ወዳጄ።

135 በቤተ ክህነታችንስ? ዛሬ ማታ ከጋዜጣ ላይ አንድ መረጃ አገኘሁ። በሎስ አንጀለስ፡ ካሊፎርኒያ፡ ብዙ የሃይማኖት አባቶች፡ ባፕቲስት እና ፕሪስባይተሪያን፡ አገልጋዮች፡ ብዙ ግብረ ሰዶማውያንን አምጥተው እነርሱን ለእግዚአብሔር ለማሸነፍ እየሞከርን ነው እያሉ፡ ግብረ ሰዶማዊነትን ይለማመዱ ነበር።

በዘመን፡ ከተከሰቱት እርግማኖች አንዱ፡ ሰዶማዊ መሆኑ ነው! ህግ እንኳን አሰሯቸዋል።

136 አሁን የት ነው ያለነው? ስርዓታችን በሙሉ ከሰራችን በሰብሷል። በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የግብረ ሰዶማውያን ቊጥር ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር በ20 ወይም በ30 በመቶ መጨመሩን አይቻለሁ። ልክ በሶዶም እንዳደረጉት፡ ወንድ ከወንድ ጋር አብሮ መኖሩን፡ አሰቡ።

137 የወንጀል መጨመር፡ የወጣት ወንጀል! በምን ዘመን ነው የምንኖረው? ዛሬ ይህ የትንቢት ቃል ተፈጸመ።

138 የሃይማኖት ዓለም፡ ቤተክርስቲያን ራሱ፡ ቤተክርስቲያን፡ የተጠራች-ቤተክርስቲያን፡ የተጠራች-ቤተክርስቲያን ብለን የምንጠራት፡ የመጨረሻዋ የቤተክርስቲያን ዘመን፡ የጴንጤቆስጤ ቤተክርስቲያን ዘመን፡ የት አለች? በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተገለጸው፡ በሎዶቅያ ነው።

139 ዛሬ ባሮቹን አውርደዋል። ሴቶቻቸው እስከ ግማሽ ለብሰዋል። ወንዶቻቸውም… በጣም አስከፊ ነገር ነው። አንዳንዶቹ በዲያቆን ቦርዶች፡ እና በሌሎች ነገሮች ሁሉ፡ ሦስት ወይም አራት ጊዜ ያገቡ ናቸው። ምክር ቤት በመመሥረታቸውና ከዓለም ጋር ቦታ በመያዛቸው፡ ውርደትና ብልሹ አደረጓቸው።

140 በዛሬው ጊዜ፡ ደግሞ፡ ከዚህ በፊት ከነበሩት ሁሉ፡ የተሻሉ ሕንጻዎችን ገንብተዋል። የሆነ ቦታ፡ አንዱ በሃምሳ-ሚሊዮን-ዶላር አዳራሽ እየገነባ ነው፡ በሃምሳ ሚሊዮን ዶላር። ጴንጤዎች! ከሃያ-አምስት ዓመታት በፊት፡ ከበሮ እየመቱ፡ አንድ ጥግ ላይ ይሰበሰቡ ነበር። እንዲህ አሉ፡ "እኛ… "

141 ምክንያቱም፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ በራእይ 3 ላይ እንዲህ ይላል፡ እንዲሁም "'ሃብታም፡' 'ሃብታም ነኝ'ና። እንደ ንግስት እቀመጣለሁ። ምንም አያስፈልገኝም፡" ብለሻል። ጎስቋላ፣ ምስኪን፣ ድሀ፣ ዕውር፣ ራቁት፣ መሆንሽን አታውቂም!"

142 ይህ ቃል ዛሬ በዓይኖቻችሁ ፊት ተፈጸመ። አሜን! **አሜን** ማለት "ይሁን" ማለት ነው። ይህ እወነት ነው አምነዋለሁ እያልኩ ነኝ እንጂ፡ ራሴን አሜን እያልኩ አይደለም። ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸም።

143 የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን በሎዶቅያ ሁኔታ ላይ ትገኛለች። ኦህ፡ ሙዚቃው ሲመታ፡ አሁንም እየዘለሉ እና እየጮሁ ይቀጥላሉ። ሙዚቃው መመታት ሲያቆም፡ ወይም አንዳንዶቹ ክርስትና ብለው የሚጠሩት ቢትኒክ ሙዚቃ አይነት፡ መጫወቱ ሲቆም፡ ክብር ሁሉ ይገፈፋል። አዎን።

144 እውነተኛ የእግዚአብሔር ውዳሴ ከሆነ ግን፡ በዓለም ላይ እሱን የሚያስቆም በቂ ፊሽካዎች——በቂ ኃይል አይኖርም። በእውነት ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ ከሆነ፡ ሙዚቃ እኪመታ ድረሰ አይጠብቅም። በላዩ ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ መውረድ ያስፈልጋል። የሚነሣው ከዚያ ነው።

145 እሱን ከረሱት እጅግ ቆይተዋል፡ ምክንያቱም የመንፈሰ ቅዱሰን ሰጦታ ማስረጃ "በልሳን መናገር የመጀመሪያ ማስረጃው ነው፡" በማለት ፈርጀውታል። እኔም ሰይጣኖች እና ጠንቋዮች በልሳኖች ሲናገሩ ሰምቻለሁ።

146 መንፈስ ቅዱስ ግን በእናንተ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ቃል ነው፡ ማረጋገጫውም ያን ቃል በመቀበል እራሱን የሚለይ ነው። ከዚያ ውጭ፡ መንፈስ ቅዱስ ሊሆን አይችልም። መንፈስ ቅዱስ ነው እያለ፡ የዚያን መጽሐፍ ቅዱስ አንዲት ቃል ቢክድ፡ መንፈስ ቅዱስ ሊሆን አይችልም። ብታምኑም ባታምኑም ማስረጃው ይህ ነው።

147 ሌላ ታላቅ ምልክት አስተውሉ። አይሁዶች በምድራቸው ውስጥ ናቸው፥ የገዛ አገራቸው፡ የገዛ ገንዘባቸው፡ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል ሆነዋል። የራሳቸው ጦር ሰራዊት አላቸው። ሁሉንም ነገር አላቸው። በትውልድ አገራቸው ውስጥ ናቸው፥ ይህም፡ ኢየሱስም "ከበለስ ዛፍ ምሳሌ ተማሩ፡" ብሎ እንደተናገረው ነው። እዚያ ናቸው፡ በገዛ አገራቸው ናቸው። እንግዲያውስ ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ፡ አይሁዶች በገዛ ምድራቸው ናቸውና።

148 ይህ ቃል የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ዛሬ ተፈጸመ።

149 ይህ ቃል፡ ማቴዎስ 24፡ ዛሬ ተፈጸመ። መላውን ዓለም፡ በጥፋት ላይ ነው፥ ህዝብ በህዝብ ላይ፡ ሮደ መሬት በልዩ ልዩ ሰፍራዎች፡ ታላላቅ አውሎ ነፋሶች ይወርዳሉ፡ ህዝቦች ይርዳሉ፡ እና ሌሎች፡ ታላላቅ አደጋዎች እየሆኑ ይገኛል። ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ።

150 አሁን የአለምን ሁኔታ አውቀናል። ተራዋ—ተራ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን፡ ድርጅት የሆነች፡ የሐይማኖት ተቋሟ፡ የት እንዳሉ አይተናቸዋል። አገሮች ሁሉ ምን ላይ እንደደረሱ አይተናቸዋል። እናም በዚህ ቀን እነዚህ ተስፋዎች ሲፈጸሙ እያየን ነው።

151 አሁን ግን፡ በዚህ ጊዜ ልዑል የሆነው፡ የአብራሃም ንጉሳዊ ዘር ይመጣል። በትክክል የሚሆነው ይህ ነው፡ ንጉስ ለሆነው ለተሰፋው ቃል ልጅ፡ ንግስት የሆነች ሙሽራ ትመጣለታለች። ትናንት ማታ እንደተናገርኩት፡ የተፈጥሮ ዘር ሳይሆን፡ መንፈሳዊ ዘር ይሆናል። መንፈሳዊ ሙሽራ ትነሳለች፡ እሷም የአብርሃም ንጉሣዊ ልጅ ንጉሣዊ እምነት ንጉሣዊት ዘር ትሆናለች። እሷም በመጨረሻው ቀን ወደ ትዕይንት ትመጣለች፡ ጊዜው እና ቦታውም ለእሷ የተሰጠ ተስፋዋ ነው።

152 እንደ ሚልኪያስ 4፡ ቅዱስ ቃል መሰረት፡ አሁንም የህዝቡን ልብ የሚያንቀሳቅስ ወደ ሐዋሪያት አባቶች የሚመለስ መልእክት ይነሳል። በዚያ ትዕይንት ላይ የሚነሳ፡ በኤልያስ ኃይል አንድ ሰው ይመጣል፡ በዚህ ትዕይንት የሚገለጥ ሰው፥ የሚመጣው የምድረ በዳ ሰው ይሆናል፡ በቀጥታ ወደ ቃሉ የሚመልስ መልዕክት ይዞ ይመጣል። እኛም እየኖርንባት ያለች ሰዓት ያቺ ናት።

153 እንግዲያውስ፡ የጀፈርሰንቪል ሰዎች ሆይ፡ አሁን በዚህች ሰዓት እጠይቃችኋለሁና፡ አሁን አስቡት። በ 1933፣ አምስት መቶ ገደማ የሚያክሉ ሰዎችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም እያጠመቅኩ በነበርኩ ጊዜ፡ ያኔ የህያ-አመት-ልጅ ሆኜ በወንዙ ላይ የወረደው መለኮታዊ ብርሃን አሰቡ። ጀፈርሰንቪል ሆይ፡ ያኔ ምን ብሎ ተናገረ? በስፕሪንግ ሰትሪት ዳርቻ ምን ተፈጠረ፡ **የኩሪየር ጆርናል፡ የሉዊስቪል ሄራልድ** ይመሰለኛል፡ መጣጥፉን በጻፈ ጊዜ ምን ተፈጠረ? ከዚያ በአሶሼትድ ፕረስ ተዘገበ፡ ከዚያም ወደ ካናዳ ተሻገረ። ዶክተር ሊ ቫይል፡ በ1933፡ በካናዳ ከጋዜጣ ቆርጦ ይዞት ነበር።

154 በዚህ ምሥክር ሥር አሥራ ሰባተኛውን ሰውዬን እያጠመቅኩ ነበር፡ እና የቀረውን ታሪክ እናንተ ራሳችሁ ታውቁታላችሁ። እኔም በዚያ ቆሜ፡ አሥራ ሰባተኛውን ሰው እያጠመቅሁ ሳለሁ፥ ብርሃን ከሰማይ ወረደ፡ ከሰማይ እንደሚወርድ ኮከብ፡ ከላይ ወደ ታች አበራ። ድምጽም እንዲህ ብሎ ተናገረ፡ "መጥምቁ ዮሐንስ የክርስቶስን የመጀመሪያ ምጽዓት አስቀድሞ እንዲያሳውቅ እንደተላከ፡ መልእክትህም፡ ዳግም ምጽአቱን ወደ ዓለም ሁሉ አስቀድሞ ይናገራል።" ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ።

155 ዛሬ ቀን! እግዚአብሔር ተስፋ ሰጠ። ምን ሆነ? የዛሬ ቀን በዓለም ዙሪያ ዞረ።

156 እግዚአብሔርም ወርዶ እንዲህ ሲል ተናገረ፡ ገና ትንሽ ልጅ ሳለሁ፡ በሚቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ፡ ወይም በእሳት አምድ በሚቃጠል፡ እዚያ ላይ በነበረው ቁጥቋጦ ውስጥ፡ በዚያ በኡቲካ ፓይክ በሚገኘው ዋተን በተባለ ሰፍራ፥ ከዚያ ጉድጓድ መጠጥ ወደሚጠመቅበት ሰፍራ፡ ከአካባቢው ውኃ ቀድቼ ሲመለስ፡ ታሪኩን ሁላችሁ ታውቁታላችሁ። "አንተ ስታድግ የምትሰራው አገልግሎት ሰላለህ፡ ፈጽመህ እንዳታጨስ፡ እንዳትጠጣ፡ ወይም በምንም መንገድ ሰጋህን እንዳታረክስ ተጠንቀቅ፡" አለኝ። እኔም ይህ እውነት እንደሆነ፡ እንዳየሁትም ምስክርነቴን እሰጣለሁ። እግዚአብሔርም፡ ከሙሴ ጋር እንዳደረገ፡ በዚያም በማኅበሩ ፊት፡ "እውነቱ ይህ ነው፡" ብሎ እንደተናገረ።

ይህ ቃል ዛሬ በመካከላችን ተፈጽሟል።

157 ሰውን ልብ ሰለመለየት ምን ብሎ እንደተናገረ፡ ምን እንደሚሆን አስተውሉ፥ እጅን በላያቸው ላይ ከመጫን አስጀምሮ፡ ውስጥ የተሰወረውን የልብ ምስጢር እስከማወቅ ድረስ። ይህ ቃል ዛሬ በዓይኖቻችን በብረቱ ፊት ተፈጽሟል።

158 የተሰጡን እነዚህ ተስፋዎች፡ አስተውሉ፡ እነዚህ ሁሉ ተስፋዎች በተሰፋው አምላክ ተፈጽመዋል እንዲሁም ተረጋግጠዋል። እነሆ፡ ዛሬ ምሽት፡ በዋሽንግተን ዲሲ ላይ፡ የተለጠፈውን፡ የጌታን መልአክ ፎቶ ተመልከቱት!

159 የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት የ FBI የጣት አሻራ እና ሰነድ ኃላፊ የሆነው፡ ጆርጅ ጄ. ላሲ፡ ከሂዩስተን፡ ቴክሳስ፡ መረመረው እና እንዲህ አለ፡ "በመላ ዓለም እስከዛሬ ከተነሱት ፎቶዎች ብቸኛው እና መለኮታዊ ፎቶ ይህ ብቻ ነው" አለ። ይህን በማድረጉ፡ በዓለም ካሉ እጅግ ምርጥ እንደሆነ፡ ሊያውቅ ይገባል።

160 አስተውሉ፡ እስራኤልን ወደ ምድረ በዳ የመራቸው ያው የእሳት አምድ፡ እንደ ምስክር፡ በዚያ ተለጥፏል። ዛሬም ተመሳሳይ መልእክት፡ ይዞ እየመራ ነው፡ ይህም፡ "ከግብጽ ውጡ!"... ? ... ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ። የተናገረውን መልእክት ታውቁታላችሁ።

161 የቱሰኑን ራዕይ አስቡ፡ የዛሬ ሶስት ዓመት፡ እዚህ መውጫው ላይ ቆሜ ሳለሁ። ከዚያም፡ ከአምስት ዓመታት ቀደም ሲል፡ እንዲህ አለ፡ "ከተማዋ ያንን ጉቶ ከዚያ ከበሩ ፊት በምትተክልበት ቀን፡ ፊትህን ወደ ምዕራብ አቅና።" እዚህ ያላችሁ የተበርናክሉ ወዳጆቼ፡ ያንን ታውቁታላችሁ-... ያን—ያን ጊዜ። በትክክል።

162 እናም ሚስተር ጎይኔስ እና ሌሎቹ መጥተው፡ ያንን ጉቶ ሲተክሉ፡ ሚስቴን "ይህ ማለት አንድ ትርጉም አለው፡" አልኳት።

እሷም “ምንድነው እሱ? ” አለችኝ፡

ገብቼም በትንሽ መጽሐፌ ውስጥ ተመለከትኩ። በዚያም አገኘሁት።

163 እና በሚቀጥለው ቀን ጠዋት፡ አስር ሰዓት ላይ፡ በዚያ በጓዳዬ፡ ተቀምጬ ሳለሁ፡ አሥር ሰዓት ላይ፡ የጌታ መልአክ መጣ። እንዲህም አለኝ፡ “ወደ ቱሰን ሂድ። በዚያም በቱሰን በሰሜናዊ ምስራቅ ትኖራለህ፡ በዚያም ሰባት መላእክት በአንድነት ይመጣሉ በዙሪያህ ያለችውን ምድር ሁሉ ያናውጣሉ።” “በዚያም ሊሆን ያለውን ነገር ይነገርሃል፡” አለኝ።

164 ከመከሰቱ፡ ቀደም ብሎ፡ ይህን የምታውቁ ሰንቶች አላችሁ? [ጉባኤው “ኣሜን፡” አለ።—አርታዒ።] ያ ነገር ሲከሰት እዚያው ቆመው የነበሩ አንዳንድ ሰዎች፡ በዚህ ህንጻ ውስጥ ዛሬ ማታ የተቀመጡ አሉ።

165 እንዲህም አለኝ፡ “የመላ መጽሃፍ ቅዱስ የተደበቁት ሰባቱ ማኅተሞች ይከፈታሉ፡ በሰባተኛው መልአክ መልእክት ሊፈጸሙ ያላቸው፡ የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 10 ነገሮች ይፈጸማሉ።” ይህ ቃል ዛሬ በዓይኖቻችን ፊት ተፈጸመ። ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ።

166 ባለፈው ዓመት፡ እዚያው ቦታ ላይ ቆሜ፡ እኔና ሚስተር ዉድ አንድ ላይ ነበርን፡ ሚስቱ ስለታመመችበት፡ አዝነን ነበርና፡ ወደ ኮረብታው ላይ እየወጣን፡ መንፈስ ቅዱስ እንዲህ አለኝ፡ “እዚያ የወደቀችውን ድንጋይ አንሣት። ወደ ላይም ወርውራት። ወደ ታች ስትመለስም፡ እንዲህ በል፡ ‘የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ እነሆ ምድርን የሚመታ ፍርድ ይወርዳል በል አለኝ።’ በሚቀጥሉት ጥቂት ሰዓታት ውስጥ፡ የእግዚአብሔርን እጅ እንደሚያይ ነገረው አለኝ።”

167 ነገሩን ለአቶ ውድ አልኩት፥ ዛሬ ማታ እዚህ አለ። ከሌሎቹ ሰዎችም፡ ስምንት ወይም አስር፡ ወይም አስራ አምስት፡ ይመስለኛል፡ በተፈፀመበት ጊዜ በዚያን ጊዜ የነበሩ አሉ፥ በማግስቱ ጠዋት፡ ጌታ በዐውሎ ነፋስ ወርዶ ተራራውን በዙሪያችን ቀደደው፡ የዛፎቹንም ጫፍ ጫፋቸውን ቆራረጠው፥ ሦስት ጊዜ አፈነዳና፡ እንዲህ አለ፡ “ፍርድ ወደ ምዕራብ ጠረፍ እየፈጠነ ነው።”

168 ከሁለት ቀናት በኋላ፡ አላስካ ከምድር በታች ልትሰምጥ ተቃረበች። እና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ መንፈሳዊ ምርመራው ላይ የመጣ የእግዚአብሔር ፍርድ፡ በዳርቻው ላይ-እና-ታች እየገነፈለ ይገኛል። የብረት መጋረጃ አለ፡ የቀርከሃ መጋረጃ አለ፡ እና የኃጢአት መጋረጃም አለ።

169 ሥልጣኔ ከፀሐይ ዙረት ጋር እንደተጓዘ ሁሉ፡ ወንጌልም እንዲሁ ነው። ልክ እንደ ፀሐይ መውጣት፡ ከምስራቅ መጥተው ወደ ምዕራብ ሄዱ። እና አሁን በምዕራብ ዳርቻ ላይ ደርሷል። ከዚህ በላይ መሄድ አይችልም፥ ወደ ፊት ከሄደ፡ እንደገና ወደ ምስራቅ ይመለሳል።

170 ነቢዩም እንዲህ እንዳለ፡ “ሌሊትና ቀን የማይባል ቀን ይመጣል፡” አሳዛኝ ቀን፡ ባለ ብዙ ዝናብ እና ጭጋግ፡ እንዴት ወደ ቤተ ክርስቲያን መቀላቀል እንደሚችሉ ወይም ስማቸውን በመጽሐፍ ላይ እንዴት ማስመዝገብ እንደሚቻል ብቻ የሚያውቁበት ቀን። “ሲመሽ ግን ብርሃን ይሆናል።” ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ።

171 በምስራቅ በኩል የምትወጣ—ያው ጸ-ሐ-ይ በምዕራብ የምትገባዋ ጸ-ሐ-ይ ራሷ ናት። እንዲሁም በምስራቅ በኩል መጥቶ ራሱን በስጋ የተገለጠ አምላክ መሆኑን ያረጋገጠው የእግዚአብሔር ል-ጅ፡ እዚህ በምዕራባዊው ንፍቀ ክበብ ያለው የእግዚአብሔር ልጅ S-o-n ራሱ ነው፡ ዛሬ ማታም በቤተ ክርስቲያን መካከል፡ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እና ለዘላለም ያው መሆኑን ራሱን እያመላከተ ነው። የልጅ የምሽት ብርሃን መጥቷል። ይህ ቃል ዛሬ በፊታችን ተፈጸመ።

172 በዚህ የአብርሃም ዘመን ላይ የት ነን? በዚህ አሁን እኛ እየኖርንበት ያለው፡ በዚህ ታላቅ ጊዜ የት እንገኛለን? ራእዮች በሙሉ ተፈጽመዋል።

173 የእኛ የእህት ቸርች ተባባሪ ፓስተራችን፡ ምስኪኑ ጓደኛችን፡ ጁኒየር ጃክሰን፡ አንድ ቀን ማታ ላይ እየሮጠ ወደ እኛ መጣና፡ ወደ እኔ መጥቶ፡ እንዲህ አለኝ፡ "ወንድምም ብራንሃም ሆይ፡ ህልም—አየሁ፡ ህልሙም እጅግ አስቸገረኝ። ሁሉም ወንድሞች በአንድ ኮረብታ ላይ ተሰብስበው አየሁ።" እንዲህም አለ፡ "አንተም በዚያ ኮረብታ ላይ፡ በዚያ ከተጻፉ ፊደሎች ታስተምረን ነበር፡ እነርሱም በዓለት ውስጥ ጊዜ የቀረጻቸው ፊደላት፡ ይመስላሉ። ያን በጨረስህ ጊዜ፡ ሁሉንም ጨረስከውና፡ እንዲህ ነገርከን፡ 'ኑ ቅረቡ፡' አልከን፡ እኛም ሁላችንም በአንድነት ተሰበሰብን።"

174 እንዲህ አለ፡ "ከሆነ ሰፍራ አንዳች ነገር አመጣህና፡ ሌባ ጎማ መሳይ፡ ያዝክና በዚያም የዚያች የትንሿ ፒራሚድ ጫፍ መታህ። እና፡ በመታኸው ጊዜ፡" አለም፡ "እነሆ በላዩ ላይ ምንም ጽሑፍ የሌለበት ግራናይት ድንጋይ ነበረ። አንተም ሁላችሁ 'ይህ ነገር ተመልከቱት' አልከን።" እኛ ሁላችሁ… "እኛም ሁላችንም መመልከት ጀመርን።" እንዲህ አለ፡ "ጭንቅላቴን መለስ አድርጌ ዞርኩኝ፡ እና ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ስትሄድ አስተዋልሁህ፡ በቻልከው ኃይል ሁሉ፡ ወደ ጸሐይ መግቢያ አቅጣጫ ሄድክ።" ሰንቶች ታስታውሳላችሁ? [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።]

175 በዚያም መንፈስ ቅዱስም እስኪገልጠው ድረስ ትንሽ ቆም አልኩኝ። እንዲህ አልኩት፡ "መጽሐፍ ቅዱስ ለሰዎች በሙላት ቢገለጥም፡ በመጽደቅ፡ በመቀደስ፡ እና በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በኩል፡ የኢየሱስ ስም ጥምቀት፡ እና እነዚያ ሁሉ ነገሮች፡ ምንም እንኳን ለሰዎች፡ የተገለጡ ቢሆንም፥ መጽሐፍ ቅዱስ በሰባት ማኅተሞች የታተመ በመሆኑ፡ አሁንም የተደበቁ ምስጢሮች ይዟል። እኔም ወደዚያ ወርጄ መፈተሽ አለብኝ።"

176 ያን ቀን ማለዳ ሰባቱ መላእክቶች ወርደው ምድርን ባናወጡ ጊዜ፡ ዓለቶችም በየአቅጣጫው በተበታተኑ ጊዜ፡ ሰባት መላእክቶች እዚያ ቆመው፡- "ወደ መጣህበት፡ ወደ ጀፈርሰንቪል ተመለስ፡ የሰባቱ ምስጢራት ሰባቱ ማህተሞች ይከፈታሉና።"

177 ይኸው፡ ዛሬ፡ **የእባቡን ዘር** እየተረዳን ነው። በጥቂት ቀናት ውስጥ፡ እግዚአብሔር ቢፈቅድ፡ ስለ **ጋብቻ እና ፍቺ** እውነቱን እንረዳለን። እግዚአብሔርም የከፈታቸው፡ እነዚህ ሁሉ ማኅተሞች፡ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የነበሩ ምሥጢራት እንረዳለን። እና በበረከቶቹ መገኘት፡ በደስታ ውስጥ ነበርን! እውነት ነው። ይህ ቃል፡ ዛሬ!

178 "ሚስጥራዊ የብርሃን ክብ ከቱክሰን እና ፊኒክስ በላይ በአየር ላይ ታየ፡" በማለት **ላይፍ** መጽሔት አንድ አንቀጽ አስነብቧል፡ ልክ ከመከሰቱ አንድ

ዓመት ገደማ በፊት፡ እንደ ትሪያንግል ሆኖ፡ እንዴት እንደሚሆን ነግሬአችሁ ነበር። ሥዕሉ አሁን እዚያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሰቅሏል። ያንን መጽሔት ያገኛችሁ ሰዎች በዚያ አሉ። በዚያ ውስጥ፡ ቁልጭ ብሏል። "ከፍታው ሃያ-ሰባት ማይሎች ሲሆን ዙርያው ሠላሳ ማይል ነው፡" ብሏል። ምን እንደተፈጠረ ገና አልተረዱም። በምስጢር ታይቶ በምስጢር ሄደ።

179 ወንድም ፍሬድ ሶትማን፡ ወንድም ጂን ኖርማን እና እኔ፡ እዚያ ቆመን ነበር፡ የሶስት ምሥክር፡ በዚያ በተራራው ላይ፥ ምስክርነታቸውን ይሰጡ ዘንድ፡ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብና፣ ዮሐንስ በዚያ እንደነበሩ፡ በዚያ ቆመን ያን ነገር ሲፈጸም ተመልክተን፡ ሲሆን አይተነዋል።

180 በዚያ፡ በሰማይ ላይ፡ እጅግ ከርቀት፡ እርጥበት በሌለበት ህዋ ላይ ተንጠልጥሎ አየነው፡ ጭጋግ——ለመሰራት የሚያስችል እርጥበት ወይም ሌላ አልነበረም። እንዴት ወደዚያ ሊመጡ ቻሉ? መልእክታቸው ካደረሱ በኋላ፡ ሲመለሱ የነበሩ የእግዚአብሔር መላእክት ናቸው። ያ ትንቢት ዛሬ በመካከላችን ተፈጸመ። ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ።

181 ተመልከቱ፡ ሰባት ማኅተሞች ተከፈተ። አውሎ ነፋሱ ወደ ምዕራብ የባህር ዳርቻ ሆነ። አሁንም፡ ያኔ ድሮ ሌሎቹ እንዳደረጉት፡ እናንተም እንዳትተላለፉት።

182 አሁን፡ ትኩረታችን፡ ወደ ዘመናችን ትንሽ እናድርግ። ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ዛሬ፡ እና ስለምንኖርበት ጊዜ ምን ይላሉ? ኢየሱስ እየተናገረ ነው… ሁሉንም ለማየት ጊዜ አይኖረኝም፡ ከመዝጋታችን በፊት ግን ይህን መዳሰስ እፈልጋለሁ።

183 ኢየሱስ በቅዱስ ሉቃስ 17ኛው ምዕራፍ፡ 30ኛው ቁጥር ተናገረ። ራሱ ቃል የሆነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ! ይህን ታምናላችሁ? ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ስጋ የሆነው፡ ቃል ራሱ፡ ቃሉ በመጨረሻው ዘመን ምን እንደሚሆን፡ የዓለም መጨረሻም ምልክቱ ምን እንደሚሆን ነገራቸው። ሕዝብ በህዝብ ላይ እንደሚነሳ ነገራቸው፡ ግን አላቸው፡ "በሰዶም ዘመን እንደ ሆነ፡ የሰው ልጅ በሚገለጥበት ቀን እንዲሁ ይሆናል።"

184 አሁን፡ ኢየሱስ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ፡ በሦስት ልጆች ስም መጣ፥ ነቢይ የሆነው፡ የሰው ልጅ፥ የእግዚአብሔር ልጅ፥ እና የዳዊት ልጅ።

185 አሁን፡ እዚህ ምድር ላይ ኖረ። በዚያም ፈጽሞ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሎ አያውቅም፡ እሱ "የሰው ልጅ ነኝ፡" አለ። ያሕዌ ራሱ፡ ሕዝቅኤልን እና ሌሎች ነብያትን፡ "የሰው ልጅ ሆይ፡" በማለት ይጠራቸዋል፡ ይህም፡ እንደ ነቢይ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመፈጸም መምጣት ስለ ነበረበት ነው። ሙሴ እንዲህ አለ፡ "አምላክህ እግዚአብሔር እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል።" የእግዚአብሔር ልጅ ሊሆን ያልቻለው ለዚህ ነው፡ ምክንያቱም እርሱ የሰው ልጅ ነበርና። እሱ… "ቃል ወደ ነቢያት መጣ፡" እርሱም ቃል በሙላት እሱ ነበር፡ የሰው ልጅ፡ ማለት——ሜጀር ነቢይ፡ ሜጀር ነበይ ሳይሆን፡ አምላክ የሆነው-ነብይ፡ "የመለኮት ሙላት በአካሉ በእርሱ ላይ ነበረ፡" ስለዚህም፡ እርሱ የሰው ልጅ ነበር።

186 አሁን፡ ላለፉት ሁለት ሺ ዓመታት፡ ለእኛ የእግዚአብሔር ልጅ በመባል የታወቀ ነበረ፡ መንፈስ።

187 እናም በሚሊኒየሙ ደግሞ፡ እሱ በዙፋኑ ላይ ሆኖ፡ የዳዊት ልጅ ይሆናል። ቅዱሳት መጻሕፍትን የምናምን ሁላችንም፡ ይህን እናውቃለን።

188 አሁን፡ በዚህ የምንኖርበት የቤተክርስቲያን ዘመን መጨረሻ ላይ፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ ማለት "በሰዶም ዘመን እንደነበረው፡ የሰው ልጅም አሁንም እንዲሁ ይገለጣል።"

189 በታሪክ ደረጃ፡ እንዴት እንዳመጣው፡ ተመልከቱት። እንዲህ አለ፡ "በእነዚያ ቀናት እንደነበረ፡" በመጀመሪያ፡ "ኖህ፡ ይበሉ፡ ይጠጡ፡ ይጋቡ፡ ያገቡም ነበር።" ቀጥሎም፡ የመጨረሻውን፡ ወደ ሰዶም፡ ወደ ሰው ልጅ፡ አመጣ። ምክንያቱም፡ በዚያ ከአይሁድ ጋር ነበር፥ እዚህ፡ በሰዶም፡ ከአሕዛብ ጋር ነው። በዚያም፡ በፍርድ፡ ሁሉንም በውኃ አሰጠማቸው፥ እዚህ፡ በአሕዛብ ላይ፡ በሰዶም ቀን ሁሉንም አቃጠለ። በትክክል። የአሕዛብ ዓለም በዚያ አረረ፡ "የሰው ልጅ ሲገለጥም እንዲሁ ይሆናል።" ከእንግዲህ ውኃ አይሆንም፡ በዚህ ጊዜ እሳት ይሆናል። ኢየሱስ ስለ ሰዶም ሲያነብ፡ ካነበብነው ዘፍጥረት 23 ላይ አንብቧል።

190 አሁን፡ ስለ ሰዶም፡ ስለ ሰዶማውያን፡ ስለ ሰዶም ሁኔታ፡ ስለ ዓለም ሁኔታ የተነገሩትን ሁኔታዎች አረጋግጠናል። እኛ፡ ሁላችንም፡ በዚህ ጉዳይ ላይ "ኣሜን" እንላለን። ያንን እናምናለን። እሺ።

191 እና የሎዶቅያ፡ ተፈጥሯዊ የሆነችው ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ስለ ሁኔታዋም፡ "ኣሜን" እንላለን፡ ምልክቶቻቸውም ተቀብለናል። እያንዳንዷ ምልክት በዚያ እንዳለች እናውቃለን። ቤተ ክርስቲያን በሎዶቅያ ላይ ናት። ያንን እናውቃለን።

192 ዓለም በሰዶም ሁኔታ ውስጥ እንዳለች እናውቃለን። ልክ ነው? ያንን እንቀበላለን።

193 ታዲያ የተሰፋውን ልጅ የሚጠብቀው፡ የአብርሃም ምልክትስ? ያ ሌላ ነበር።

194 አስታውሱ፡ ያኔ ሶዶም ነበረ፥ መልእክተኛም ነበራቸው። ለአብራሃምም የራሱ መልእክተኛ ነበረው።

195 አብርሃም፡ ሊሆን የማይችል ነገር እንዲሆንለት እየጠበቀ፡ ከቀን ወደ ቀን፡ ቆየ። "ሣራ፡ ዘጠና፡ እርሱም መቶ አመት።" እንደ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን መሰረት፡ አሁንም እየጠበቀ ነበር። በሁሉም ትችቶች መካከል፡ ያንን ልጅ ይጠባበቅ ነበር።

196 አሁንም እውነተኛው አማኝ ያ ተሰፋ የተገባለት ልጅ ተመልሶ እስኪመጣለት ድረስ እየጠበቀ ነው! ልብ በሉ፡ ልጁ ከመምጣቱ አስቀድሞ፡ ምልክት ተሰጠው። አብራሃም የፍጥረታዊው ልጅ እንደ ወለደ የመጪው ልጅ ምልክት ለአብርሃም ንጉሣዊ ዘር፡ ንጉሣዊውን ልጅ ለሚጠባበቀው ዘር ሊገለጥ ምልክቱ አይደለምን? ትክክል? ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ እዚህ በቅዱስ ሉቃስ 17፡30 ላይ፡ "ይህ ጊዜ ከመምጣቱ በፊት፡" ይህም "ሰዶም ከመጥፋቷ በፊት፡ የሰው ልጅ በሰዶም ዘመን እንዳደረገው ይገለጣል" ማለት ነው። አሁን ምልክት እየጠበቅን ነው።

197 አሁን በሰዶም እንደነበረው በዘመኑ የነበሩ ሁኔታዎችን እንውሰድ። ልብ በሉ፡ ሁሉም ከሰዶማዊት ዓለም፡ ወጡ።

198 ከፊልሙ ዓለም ዳይሬክተሮች አንዱ በቅርብ ጊዜ፡ የቀረጸው ምስል አለ፡ እኔም አይቼዋለሁ፡ ያም፡ **ሰዶም** ናት። ካያችሁት በቀር ሌላ ነገር ከሌለው፡ አስተውላችሁ ተመልከቱት። ዛሬ ካሉት የዮናይትድ ስቴትስ ፊልሞች እጅግ መልካም ምስል ነው፡ የሆሊዉድ፡ በትክክል፡ ያኔ የነበረውን ተመሳሳይ ልብሰ እና ሌላ ነገር ሁሉ፥ ትላልቅ ሰካራሞች እና ሌሎች ነገሮች ሁሉ፡ ሃይማኖታዊ የሰዎች አምልኮ፡ ሃይማኖታዊ-ተብየው።

199 ልብ በሉ፡ ሰዶም ምስክር ነበራት፡ እሱም ሎጥ የተባለው ግለሰብ ነው፡ እሱም ለ—ለአብራሃም የወንድሙ ልጅ ነበር።

200 አሁን፡ አብርሃም እሱና ሰራዊቱ፡ ወደ ሰዶም አልወረዱም። ከእሱ ጋር አንድ ትልቅ ሰራዊት ነበረ፡ ደርዘን የሚጠጉ ነገሥታትን እና ሠራዊታቸውን መግጠም የሚችል በቂ ሰራዊት ነበረው። ስለዚህ፡ ከእርሱ ጋር ታላቅ ሰራዊት ነበረው። በዚያም ከአድባር ዛፍ ሥር ተቀምጦ፡ አንድ ቀን፡ ሰው ሁሉ ርቆታል፥ ማንም ከእሱ ጋር አይተባበርም ነበር፡ እሱ ግን አሁንም የተሰፋ ቃሉን አጥብቆ ይዞ ነበር።

ከመዘጋታችን በፊት፡ አሁን፡ በደንብ ተመልከቱ።

201 በዚያ ተቀምጦ ሳለ፡ ሦስት ሰዎች፡ ወደ እርሱ እየተራመዱ መጡ። ከእነርሱም ሁለቱ ወደ ሰዶም ወረዱ በዚያም ሎጥን፡ ውጣ በማለት፡ ወንጌልን ሰበኩላቸው። ልክ ነው፣ አንዱ ግን ከአብርሃም ጋር ቀረ። ልብ በሉ፡ ከአብርሃም ጋር የቀረው እግዚአብሔር ራሱ ነው። ሌሎቹ ሁለቱ መላእክት መልእክተኞች ናቸው።

202 አሁን፡ በሰዶም ወርደው፡ ዓይን ከማሳወር በቀር፡ ምንም ተአምር አላደረጉም። ወንጌልን መሰበክ ደግሞ ሁል ጊዜ እውር ያደርጋቸዋል።

203 አሁን በወቅቱ የነበረ የዘመኑ አሰላለፍ ተመልከቱት። ፍጥረታዊት ቤተ ክርስቲያን አለች። ባለፈው ምሽት እንዳልኩት፡ እግዚአብሔር፡ ሁሉ ጊዜ በሶስቶች ይከናወናል። ሰዶማውያን፡ ሎጣውያን፡ እና አብረሃማውያን ነበሩ። ዛሬ ምሽትም ዓለም እና ሁኔታዋ፡ በተመሳሳይ መልክ ትገኛለች።

204 አንድ ነገር ልጠይቃችሁ። አሁን ይህን ሂደት ተመልከቱት። አብርሃም ይህን የተናገረውን ሰው "ኤሎሂም፡" አለው። **ኤሎሂም** የሚለው የዕብራይስጥ ቃል "ምንም የማይሳነው፡ ዘላለማዊ የሆነው፡" ኤሎሂም፡ እግዚአብሔር ራሱ ማለት ነው!

205 በመጀመርያ፡ ኦሪት ዘፍጥረት 1 ላይ፡ ሲናገር፡ "በመጀመሪያ እግዚአብሔር… " እዚህ ላይ የዕብራይስጥ ቃል፡ ወይም፡ የግሪክ ቃል፡ ማለቴ ነው፡ "በመጀመሪያ **ኤሎሂም** ሰማይንና ምድርን ፈጠረ።"

206 እዚህ፡ እሱ፡ እንደገናም፡ በዘፍጥረት፡ 22 ላይ፡ ወይም—ወይም 20 ላይ፡ እንዲህ አለ፡ የዚህንም ሰው ስም "ኤሎሂም" ብሎ ጠራው። ለምን ጠራው? እግዚአብሔር፡ በሰው ሥጋ ስለተመሰለ፡ ከአብርሃም ጋር ተቀምጦ የጥጃ ሳንድዊች በላ፡ ወተት ጠጣ፡ እንጀራ በላ። እግዚአብሔር ራሱ፡ አሁንም ከአብርሃም ፊት ተሰወረ።

207 ነገር ግን ምልክት ሰጠው። ልብ በሉ። ምልክቱም ደግሞ ጀርባውን ወደ ድንኳኑ እንዳዞረ የሚያሳይ ምልክት ነው።

208 አስታውሱም፡ ከዚያ ቀን ጥቂት ቀናት በፊት፡ አብራሃም ስሙ **አብራም** ይባል ነበር፡ ሣራም **ሣራይ** ትባል ነበር፡ S-a-r-r-a በኋላ ግን S-a-r-a-h፣ እና A-b-r-a-m በኋላ A-b-r-a-h-a-m ተባለ። **አብርሃም** ማለት "የህዝብ አባት" ማለት ነው።

209 አሁን እዚህ ላይ በደንብ ተከታተሉ፡ እኛ የየኖርንበት ባለው በዚህ ወቅት ውስጥ ያሉ ክንዋኔዎችን እንመለከታለን፡ ኢየሱስ ይህንን ክንዋኔዎችን እንድንጠባበቅ ነግሮናል። ሌላውን ሁሉ በትክክል አይተናል፥ አሁን ወደ ንጉሣዊው ዘር፡ ምን ዓይነት ክንዋኔ ማየት እንዳለባቸው እንመልከት።

210 አሁን ይህ ሰው እንዲህ አለው፡ "አብርሃም ሆይ፡ ሚስትህ ሣራ፡ ወዴት ናት? "

አብርሃምም "በድንኳኑ ውስጥ፡ ከኋላህ አለች፡" አለው።

211 አሁን፡ ከዚህ በፊት አይቷት አያውቅም። ስሙ **አብርሃም** መሆኑን እንዴት አወቀ? ሰሟ **S-a-r-a-h** መሆኑን እንዴት አወቀ? "አብርሃም ሆይ፡ ሚስትህ ሣራ፡ ወዴት ናት? "

"ከበስተጀርባህ፡ በድንኳኑ ውስጥ ናት፡" አለው።

212 እንዲህ አለው፡ "እኔ... " "እኔ፡" ሲለው የግል ተውላጠ ሰም። "በገባሁላችሁ ቃል መሰረት ልጎበኛችሁ ነው። ሚስትህ ያንን ልጅ ትወልዳለች። አንተ አምነኸኛልና፡ አሁን እንዲፈጸም አደርገዋለሁ።"

213 ሣራም፡ በድንኳኑ ውስጥ፡ ከኋላ፡ ጀሮ ጠቢ ወይም ጆሮዋን ሰክታ ስትሰማ፡ የፈለጋችሁት በሉት፡ በድንኳኑ ውስጥ እየሰማች፡ እጅጌዋን ሰብሰባ ሳቀች፡ እና እንዲህ አለች፡ "አሁን፡ እኔ አሮጊቷ ሴት፡ እሱም፡ አዛውንት ሆኖ፡ ደግሞ፡ አንድ መቶ ዓመት ከሞላው፡ ከጌታዬ ጋር ደስ ይለኛልን? እንደውም፡ ይህን ማድረግ ከተውነው፡ ብዙ ብዙ ዓመታት አልፏል አለች።"

214 ሰውዬውም፡ M-a-n፡ በዚያ እየበላ፡ የሰው ሥጋ ለብሶ፡ እንደ ተራ ሰው እየጠጣ እና እየበላ፥ ልብሱ ላይ ትቢያ ነበረ፥ እግሩም ትቢያ ነበረው፥ አብርሃምም አጠበው። እግዚአብሔር፡ ራሱ፡ ዘወር ብሎ፡ እንዲህ አለ፡ "ሣራ በድንኳኑ ውስጥ ሆና፡ **እንዲህ** ስትል፡ ለምን ሳቀች? " ከኋላው የነበረችውን፡ የሣራን የልብ አሳብ መለየት፡ ማወቅ ችሏል። ልክ ነው?

215 እንግዲህ፥ የአብርሃም ንጉሣዊ ዘር ወደ ምድር ሲመጣ፡ ምን ምልክት አሳይቷል? የሰው ልጅ። ስምዖን አንድ ቀን እንድርያስ አመጣውና፡ ወደ እርሱ መጣ። እርሱም፡ "ስምህ ስምኦን ይባላል። አንተ የዮናስ ልጅ ነህ፡" አለው። አያችሁ፡ ያ ነገር ከውሰጡ አማኙን አፈራለት።

216 ፊልጶስም ሄዶ፡ ናትናኤልን ይዞ መጣ። "ና፡ ያገኘነውን ሰው ተመልከት—የዮሴፍን ልጅ፡ የናዝሬቱን ኢየሱስን፥ አግኝተነዋልና፡" አለው።

217 እሱም፡ "እስኪ ቆይ አንዴ። ከዚያ ከአክራሪነት ጥሩ ነገር ሊወጣ ይችላልን? "

"ና፡ እይ፡" አለው።

218 ፊልጶስም ከናትናኤል ጋር፡ ወደ ኢየሱስ ፊት በቀረበ ጊዜ፡ ኢየሱስ ወደ እርሱ ተመልክቶ "እነሆ ተንኰል የሌለበት እስራኤላዊ፡" አለ።

እርሱም አለው፡ “መምህር ሆይ፡ ከወዴት ታውቀኛለህ? ”

219 “ፊልጶስ ሳይጠራህ፡ ከዛፉ ሥር ሳለህ፡ አየሁህ፡” አለው።

220 እርሱም አለው፡ “መምህር ሆይ፡ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ። አንተ የእስራኤል ንጉሥ ነህ!”

221 በጉድጓድ አጠገብ የነበረችው ሴት፡ በብልሹ ሥነ ምግባር ሆና፡ ውኃ ቅጂልኝ፡ የሚል ትዕዛዝ መሳይ ነገር፡ መጣባት። ኢየሱስ ግን ምግብ ሊገዙ፡ ደቀ መዛሙርቱን ልኳቸው ነበር። ውኃ ልትቀዳ በወጣች ጊዜ፡ “አንቺ ሴት፡ ውኃ አጠጪኝ፡” አላት።

222 እንዲህ አለችው፡ “እንዲህ ማለትህ ልምዳችን አይፈቅድልህም። በመካከላችን ልዩነት አለ። እንግዲህ፡ እናንተ አይሁዶች ከእኛ ከሳምራውያን ጋር ምንም የላችሁም፥ ከአንተ ጋር ምንም ግንኙነት የለንም።”

223 እርሱም፡ “አንቺ ሴት፡ ከማን ጋር እንደምትነጋገሪ፡ ብታውቂ ኖሮ፡ አንቺ ራስሽ የሚጠጣ ትጠይቂኝ ነበር። ወደዚህ መጥተሽ እንዳትቀጂም እኔ ውኃ በሰጠሁሽ ነበር።”

224 ሁኔታዋ የት እንዳለ፡ ምን እንደሆነ አገኛት። “ባልሽን ይዘሽ ወደዚህ ነይ፡” አላት።

“ምንም ባል የለኝም፡” አለችው።

225 እሱም “እውነት ተናግረሻል። አምስት ባሎች ነበሩሽ፡ አሁን አብረሽ ያለሽውም ባልሽ አይደለም፡” አላት።

226 እሷም አለችው፡ “ጌታዬ፡ ነብይ እንደሆን አያለሁ። መሲሑ ሲመጣ እነዚህን ነገሮች እንደሚያሳየን እናውቃለን።”

ኢየሱስም “እኔ እሱ ነኝ፡” አላት።

227 በዚያውም፡ ወደ ከተማ ሮጠች እንዲህም አለች፡ “ያደረግሁትን የነገረኝን ሰው፡ ኑና እዩ። ይህ ራሱ መሲሕ አይደለምን? ”

228 ተመለከቱ፡ ያን ያደረገው በሳምራውያን እና በአይሁድ ፊት ብቻ ነው፡ በአሕዛብ ፊት አላደረገውም። እኛ ሰዎች፡ እኛ አሕዛብ፡ በዚያ ዘመን አረማውያን ነበርን፡ ሌሎች ሕዝቦች ነበርን፡ ጀርባችን ላይ እንጨት የተሸከምን፡ ጣኦት አምላኪዎች ነበርን። መሲሕን አንጠብቅም ነበር።

229 የተገለጠው እርሱን ለሚሹት ብቻ ነው፡ እኛም እርሱን መፈለግ ነበረብን።

230 እርሱን እንፈልገዋለን የሚሉት ግን፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ እራሷ፡ ይህን ሲሆን እየተው፡ እንዲህ አሉ፡ “እሱ ሰይጣን ነው። ሟርተኛ ነው፡ ብዔልዜቡል!”

231 ኢየሱስም አለ፡ እሱ ገና አልሞተምና፡ “ያ ኃጢአት ይሰረይላቸዋል” አለ። “ግን፡” አላቸው፡ “አንድ ዘመን መንፈስ ቅዱስ ይመጣል እና ያን ጊዜ ብትሳደቡ፡ እሱን የሚጻረር አንዲት ቃል የሚናገር ይቅርታ የለውም።” ዘመኑ አሁን ነው፡ እያንዳንዱ ቃል በአንድነት የሚገጣጠምበት ጊዜ ይህ ነው። “በእርሱ ላይ አንድ ቃል የሚናገር፡ በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም ፈጽሞ ይቅር አይባልም።”

232 የአብርሃም ንጉሣዊ ዘር ያ ነው። የአብርሃም ንጉሣዊ ዘር ይህ ነው፡ ይህም ከአብርሃም ጋር ተቀምጦ በነበረውን ሰው ምንነት የተገኘ ነው፡ አሁንም ይህ

አምላክ እሱ መሆኑ ለማረጋገጥ፡ በዚህ ዘመን ቃል ገባ፡ “በሰዶም ዘመን እንደነበረ፡ በሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል፡ የሰው ልጅ ሆኖ ራሱን በገለጠበት ጊዜም እንዲሁ ይሆናል።” አሜን። ቃሉ የሚፈጸምበት ቀን ይህ ነው።

233 ዛሬ ያለንበትን ክንዋኔዎቹን ተመልከቱ። የእግዚአብሔር ልጅ ያለበትን ቤተ ክርስቲያን ተመልከቱ... እስከፊውን ቀን ተመልከቱ። ሁሉንም ትንቢቶች ተመልከቱ። አሁን፡ የሚገርም ነገር፡ ክንዋኔዎቹ እንደ ሰዶም መሆን ካለባቸው፡ እንግዲያውስ ኅብኚዎቻችን የሚመጡበት ወቅት አሁን ነው።

234 ሦስቱም ከሰማይ የተላኩ፡ ሦስት ታላላቅ ሰዎች አብረው መጡ። ያንን እናውቃለን። ሦስቱ፥ አንዱ ከአብርሃም ጋር ቀረ። ሁሉም አጀማመራቸው ከዚያ ነው፡ አንዱ ግን ከአብርሃም ጋር ቀረ። ሌሎቹ ግን ወደ ሰዶም ወረዱ። ልክ ነው? አብራሃምም የስም ለውጥ ተደረገለት፡ ከአብራም አብራሃም ተባለ። ልክ ነው?

235 የዓለም ቤተክርስቲያን፡ እስካሁን ድረስ በታሪክ ውስጥ፡ እንዲህ አይነት ወንጌላዊ ተልኮላት አያውቅም ነበር፡ የስሙ መጨረሻ ሃ-ም የሆነ ሰው፡ ቢሊ ግ-ራ-ሃ-ም፡ እስከዛሬ ድረስ ተልኮ አያውቅም። ልክ ነው? G-r-a-h-a-m፣ ባለ ስድስት ፊደሎች። A-b-r-a-h-a-m ባለ ሰባት ፊደላት ነው። G-r-a-h-a-m ግን ባለ ስድስት ፊደላት ነው፡ እሱም ዓለም፡ ሰው ነው። አያችሁ?

236 ዛሬም፡ የወጡትን ነገሮች ተመልከቷቸው፡ እነዚያ መልእክተኞች ከሰማይ መጡ።

237 በምድር ላይ እንደ ቢሊ ግራሃም በግልፅ ንሰሃ ስለመግባት የሰበከ ሰው አለን? እንደ ቢሊ ግራሃም፡ በሰዎች ላይ ተጽእኖ ያሳደረ ሰው አለን? በአለም አቀፍ ደረጃ፡ አንድም ሰው፡ አልነበረም። ኦህ፡ ቢሊ ሰንደይ፡ እና ሌሎች፡ እዚህ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ አሉ፡ ቢሊ ግራሃም ግን በዓለም ዙሪያ ይታወቃል። ከየት እየተጣራ እንዳለ አይታችኋል? ከሰዶም።

238 ከኦራል ሮበርትስ፡ ከጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ጋር ጎን ሎጎን እየተጓዘ ይገኛል።

239 ታዲያ ምርጦቹስ? ምን አይነት ምልክት ያያሉ? ምን ሊኖራቸው ይገባል? ሃሌ ሉያ! “ሲመሽ ብርሃን ይሆናል።” ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ። የእግዚአብሔር ተስፋ ቃል ዛሬ ተፈጸመ። ይህ እውነት እንደሆነ እናውቃለን። ድሮ እንደነበረ ዛሬ ምሽትም እዚህ ነው።

240 አሁን፡ ሰትሰብኩ፡ አስቀድሜ እንደተናገርኩት፡ ማንኛውም ነገር ሰትሰብኩ የሰበካችሁት ነገር የወንጌል እውነት ከሆነ፡ እግዚአብሔር ያንን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት። ልክ ነው? እንግዲህ፡ ይህ እውነት ከሆነ፡ ቃሉን የጻፈው ይህ አምላክ፡ ትንቢቱን የተናገረው ያ አምላክ እንዲህ ያድርግ፡ የቃሉ አምላክ የሆነው አምላክ፡ ይውጣና አሁንም አምላክ መሆኑን ያስመሰክር።

241 ኤልያስ ወደ ተራራው ሲወጣ፡ ኤልሳዕም እየተመለከተ፡ ኤልያስን እያየ ወጣ፡ “በእጥፍ እፈልጋለሁ፡” አለ። የኤልያስ መጎናጸፊያም በኤልሳዕ ላይ ወደቀ። እሱም ወርዶ፡ መጎናጸፊያውን በድርብ አጠፈውና፡ “የኤልያስ አምላክ ወዴት ነው? ” አለና ወንዙን መታው፡ በኤልያስም ላይ የሆነው ተመሳሳይ ነገር፡ በኤልሳዕ ላይ ሆነ።

242 ትናንትም የነበረው ያው ወንጌል፡ ያው ኃይል፡ ያው የሰው ልጅ፡ ዛሬም፡ ለዘላለምም ያው ነው። ዕብራውያን 13፡8። ታምናላችሁ? [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።] እንግዲያውስ፡ ጠየቅኳችሁ። እኔ እርሱን መሆን አልችልም፡ እርሱ ግን እዚህ አለ። እኛ ተሸካሚዎች ብቻ ነን።

243 እዚያ ያላችሁ አንዳንድ ሰዎች፡ የታመማችሁ እና የተቸገራችሁ ሁሉ፡ እኔ እንደማላውቃችሁ የምታውቁ ሰዎች፡ እግዚአብሔር አሁን እንዲህ ያድርግላችሁ... ራሴን በበቂ ሁኔታ ትሁት ካደረግኩኝ። ጸልዩ እግዚአብሔርንም ለምኑ።

244 እንጃ... በህንፃው ውስጥ የጸሎት ካርድ አልታደለም፡ አይደል? አይ፡ አይመስለኝም... የጸሎት ካርድ ፈጽመን አልሰጠንም። የጸሎት ክፍለ ጊዜ፡ የታመሙትን ፈውስ፡ በዚህ ቤተ ክርስቲያን... እናደርጋለን። እናንተ ግን፡ ጸልዩ።

245 እኔ ለእናንተ ፍጹም እንግዳ መሆኔን ታውቃላችሁ። እያችሁ፡ ከጀፈርሰንቪል መሆኔን፡ ታውቃላችሁ! ከጄፈርሰንቪል በመጡ ሰዎች ላይ ይህን ማድረግ አልፈልግም። ከዚያ የራቁ ከዚህ አካባቢ የሆኑ ሰዎች እፈልጋለሁ። እግዚአብሔር አሁንም ይገልጥ እንደሆነ እዩ! እርሱ አሁንም ትናንት፡ ዛሬ፡ እና ለዘላለም ያው እንደሆነ እዩት!

246 ሴቲቱ እንዳደረገችው አድርጉ። እያለፈ ነበርና፡ "ይህን ሰው አምነዋለሁ፡" አለች። የደም ችግር ነበራት፡ እና እንዲህ አለች፡ "የልብሱን ጫፍ ከነካሁ፡ ጤነኛ እሆናለሁ ብዬ አምናለሁ።" ልክ ነው?

247 በእምነቷ ምክንያት፡ በዚያ ቀን፡ ቃሉ ተፈጸመ። "የተሰበረውን ልብ ጠግኗል፡ የታመሙትንና እንካሶችን ፈውሷል።"

248 ልብሱን ዳሰሳ ሄደችና፡ ከተቀመጠች በኋላ፡ ዞር ብሎ "የነካኝ ማን ነው፡" አላቸው? በዚያ ታላቅ ሕዝብ መካከል፡ በሺዎች በሚቆጠሩ፡ ምናልባት ዛሬ ማታ እዚህ ካለ ይልቅ በሰላሣ ዕጥፍ ይበልጣል፡ እንዴት ሊያውቅ ቻለ? እንዴት አወቀ? "የነካኝ ማን ነው፡" ብሏልና? ስለ ማለት ብቻ ያንን አላለም፥ እውነት ስለሆነ ግን ተናገረ። "የነካኝ ማን ነው፡" ብሎ ጠየቃቸው? በቀጥታም ዘወር ብሎ ተመለከተና ሴቲቱ እያት፡ ተቀምጣም ይሁን ቆማ ነበረች፡ በምንም አይነት ሁኔታ ትሁን፡ ከደም ችግር እንደተፈወሰች ነገራት።

249 ያ ኢየሱስ በትናትና ነው። ዛሬም ያው ነው። ታምናላችሁ?

250 እኔ አላውቅህም፥ እግዚአብሔር ግን ያውቅሃል። በጎንህ በኩል ህመም አለብህ፡ እጅግ ያስቸግርሃል። በትክክል። እዚህ ተቀምጠህ የምትጸልየው ስለዚያ ነው። እኔ ለአንተ እንግዳ እንደሆንኩ ሁሉ፡ ሁለታችንም እንግዳማቾች አይደለንምን? ከሆንን፡ ተነስተህ ቁም። እኔ አላውቅህም። **እዚያ** ጥግ ላይ ያለው ይህ ሰው ነው፡ ይህ ወጣት ሰው። አንተም ጉሮሮህ እጅግ አሞሃል። ትክክል ነው። ስለዚያ እየጸለይክ ነው። በአንድ ነገር እጅግ ትጨነቃለህ። ከጉባኤው ትሄዳለህ፡ አንተም አገልጋይ ስለሆንክ፡ ልታደርጋቸው የሚገቡህ አንዳንድ ነገሮች አሉ። በትክክል። ኧሃ-ሃህ። እግዚአብሔር ማን እንደሆንክ እንደሚያውቅህ ታምናለህ? ሬቨረንድ ሚሰተር ሰሚዝ ትባላለህ፡ አሁን ሂድና ተፈወስ። ኢየሱስ ክርስቶስ ፈውሶሃል። ወደ ጉባኤህ ሂድ፡ ጉሮሮህ አያስቸግርህም።

ማንን ነክቶ ነው?

251 **እዚህ** አንድ ሰው ተቀምጧል፡ እየተሰቃየ ነው። በግራ ሳንባው ላይ ዕጢ አለበት። ከዚህ… ከአካባቢው አይደለም። የማዕድን ሰራተኛ ነበርክ። ልክ ነው። እኔ ለአንተ ሙሉ በሙሉ እንግዳ ነኝ። ያ ትክክል ከሆነ፡ እጅህን አወዛውዝ። ዕጢው በግራ ሳንባህ ውስጥ ነው፡ እና ወዲያውኑ ቀዶ ጥገና ሊደረግልህ ነው። ልክ ነው? ከዚህ አካባቢ አይደለህም። ከከተማው ውጪ ነህ። ከቨርጂኒያ ነህ። በትክክል። እግዚአብሔር ማን እንደሆንክ እንደሚያውቅህስ ታምናለህ? ሚስተር ሚሽል፡ ልክ ነው፡ ወደ ቤት ሂድ እና ደህና ሁን። ኢየሱስ ክርስቶስ ፈውሶሃል። ሰውየውን ጠይቁልኝ! በሕይወቴ፡ አይቼው አላውቅም። በዚያ ተቀምጦ፡ ይጸልይ ነበር።

ይህ ቃል ዛሬ!

252 ሣራ በድንኳኑ ውስጥ እንደነበረች፡ ከኋላዬ፡ አንዲት ሴት እዚህ ተቀምጣለች። ስለ ሴት ልጇ እየጸለየች ናት። ተነሺ። ልጅሽ እዚህ የለችም፥ ሴት ልጅ፥ ያለችበት ሩቅ ነው። አንቺም ወደ ኢየሱስ እንደመጣች እንደዚያች ሴት ነሽ፡ እሷም እጅግ የተሰቃየች ሴት ነበረቻት። የሴቲቱ… ሴት ልጇ በዲያብሎስ ተይዛ ነበርና። እሷም እዚህ የለችም። እሷ ከ… አንቺም ከሰሜን ካሮላይና ነሽ። አመንሽ? እውነት ነው፡ አይደል? ወይዘሮ ኦርደርስ፡ ወደ ቤትሽ ሂጂ። በሙሉ ልብሽ ካመንሽ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በጥንት ጊዜ ተፈውሳለች ብሎ እንደተናገረ፡ አንቺም ልጅሽ ተፈውሳ ታገኛታለሽ።

253 ይህ ቃል ዛሬ፥ የሰዶም ምልክት፡ የልዑሉ ዘር ምልክት፡ የፍጥረታዊት ቤተ ክርስቲያን ምልክት! ይህ ቃል ዛሬ በመካከላችሁ ተፈጸመ። ታምናላችሁን?

254 አሁኑኑ እንደ አዳኛችሁ እና እንደ ፈዋሻችሁ ትቀበሉታላችሁን? ሁላችሁም፡ በእግሮቻችሁ ቁሙና፡ እንዲህ በሉ፡ “ፈውሴን ተቀብያለሁ። እርሱን እንደ አዳኜ ተቀብያለሁ። ንጉሤ አድርጌ ተቀብዬዋለሁ።” እያንዳንዳችሁ በእግሮቻችሁ ቁሙ።

በዚህ ቀን! አድምጡኝ፡ ወዳጆች ሆይ።

255 “ቃሉን አንብቦ፡ መጽሐፍ ቅዱስን ለካህኑ ሰጠው፡ እና፡” ይላል፡ “የሕዝቡም ዓይኖች ሁሉ በእርሱ ላይ ነበሩ። እርሱም ትኩር ብሎ አያቸውና፡ እንዲህ አላቸው፡ ‘ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ።’”

256 በመጨረሻው ቀን እንደምንኖር፡ በደርዘን ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ማስረጃዎች፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር በሚመለስበት ትውልድ ላይ እየኖርን እንዳለ አንብቤአለሁ። ዛሬም እንደገና፡ እላችኋለሁ፡ ይህ ቃል ዛሬ በአይኖቻችሁ ፊት ተፈጸመ።

257 በቱክሰን፣ በካሊፎርኒያ፣ በኒውዮርክ ውስጥ፣ በሰልክ-መስመር ውስጥ ያላችሁ ሁላችሁ፡ ይህ ቃል ዛሬ በአይኖቻችሁ ፊት ተፈጸመ እላችኋለሁ።

258 የበጉ ሰርግ ቀርቦአልና ደስ ይበለን፡ ሐሤትም እናድርግ። ሙሽራዋ… ሙሽራይቱም ራሷን አዘጋጅታለች።

259 ሁላችሁም ሰዎች ሆይ፡ እጆቻችንን ከፍ እናድርግ እና ክብር እንስጠው። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

65-0219 ይህ ቃል ዛሬ ተፈጸመ
ፓርክቪው ጁኒየር ሀይ ስኩል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org